አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድኅረ ምረቃ ት/ቤት
የሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ
በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

# አሊጎሪ በአማርኛ ዘመናዊ አጫጭር ልቦለዶች

በ

እንዳለጌታ ከበደ

ህዳር 2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድኅረ ምረቃ ት/ቤት

የሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ

በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

# አሊጎሪ በአማርኛ ዘመናዊ አጫጭር ልቦለዶች

በ

እንዳለጌታ ከበደ

አማካሪ

አብርሃም አለሙ (አቶ)

ህዳር 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድኅረ ምረቃ ት/ቤት

የሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ

በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

# አሊጎሪ በአማርኛ ዘመናዊ አጫጭር ልቦለዶች

በ

እንዳለጌታ ከበደ

## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| | | |

አማካሪ

| ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| ቴዎድሮስ ገብሬ | | 20/07/04 |

ፈታኝ

# ምስጋና

ይህን ጥናት በምሰራበት ጊዜ፣ ብርታት ሲለግሰኝ ለቆየው ለአማካሪዬ ለአቶ አብርሃም አለሙና የምርምር ሃሳቡን በመፈንጠቅ ለተባበሩኝ ለተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው ምስጋናዬ የበዛ ነው፡፡

የአሊጎሪን ምንነት እንዲገባኝ ላደረጉትና የመረጃ ምንጮች ለጠቆሙኝ ለዶክተር ዮናስ አድማሱ፣ በጉዳዩ ላይ የተጠኑ ሥራዎችን በማቅረብ አይዞህታው ላልተለየኝ አብሮ ተማሪዬ ሙሉቀን ንጋቱ፣ ስንፍና ተጫጭኖኝ ጥናቴን ቸል እንዳልለው ትጎተጉተኝ ለነበረችው ለባለቤቴ እሌኒ መስፍን ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

# አጠቃሎ

‹አሊጎሪ በአማርኛ ዘመናዊ አጫጭር ልቦለዶች› በሚል ርዕስ የቀረበው ይህ ጥናት የአሊጎሪን ምንነትንና ጠቀሜታን፣ የአሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት በአለም ሥነ ጽሑፍ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ያለውን ቦታ ምን እንደሚመስል እና አሊጎሪ በአማርኛ ቋንቋ በተጻፉ አጫጭር ልቦለዶች ውስጥ የተሰጠውን ቦታ ማሳየት አላማ አድርጎ የተነሳ ነው፡፡

ጥናቱ አራት ምዕራፎች አሉት፡፡ ምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን እና የጥናቱ ዘዴ ይዟል፡፡ በምዕራፍ ሁለት ላይ ክለሣ ድርሣን የቀረበ ሲሆን፤ ይህም በንድፈ ሃሣባዊ ቅኝት ሥር የአሊጎሪን ምንነት፣ ጠቀሜታንና አሊጎሪ በአማርኛ ሥነጽሁፍ ሥራዎች ውስጥ ተዳሰሰዋል፡፡ ምዕራፍ ሦስት አሊጎሪ በአማርኛ ዘመናዊ አጫጭር ልቦለዶች የሚል ርዕስ የሚከተል ሲሆን በርዕሱም በአምስት ደራስያን የተደረሱ 7 አጫጭር ልቦለዶች ቀርበዋል፡፡

ከስብሃት ገብረ እግዚአብሔር *አምስት ስድስት ሰባት* ከተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ ሁለት ልቦለዶች፣ ከአዳም ረታ *ማህሌት* እና *አለንጋና ምስር* ከተሰኙ ሁለት መጻሕፍት ውስጥ ሁለት ልቦለዶች፣ ከአሳምነው ባረጋ *የትሮይ ፈረስ* መጽሐፍ ውስጥ አንድ ልቦለድ፣ ከአለማየሁ ገበየሁ *የአበሻ ፊት* ውስጥ አንድ ልቦለድ እና ከሚካኤል ሺፈራው *የወፍ ማስፈራሪያ* ውስጥ አንድ ልቦለድ በአጠቃላይ ሰባት አጫጭር ልቦለድ ልቦለዶች ከአሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት አንጻር ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

በመሆኑም አጫጭር ልቦለዶቹ በሰውኛ አቀራረብ የተሳሉ ገፀ ባህሪያትን በመጠቀም ሃይማኖታዊ፣ ሞራላዊ፣ ሥነ ምግባራዊ እና ፖለቲካዊ መልዕክቶች በአሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት አማካኝነት አቅርበዋል፡፡ እንዲሁም በልቦለዶቹ ውስጥ ትዕምርቶች፣ ምልክቶችና ተነፃፃሪ ዘይቤዎች አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ ደራስያኑ እንደ አውራ ዶሮ ያሉ እንስሳትን፤ እንደ ወራት ያሉ ረቂቅ ነገሮችን፤ እንደ ወንበር ያሉ ግዑዝ እቃዎችን፣ እንደ ዛፍ፣ አበባ፣ ድንች ያሉ ተክሎችን እና እንደ ቢራቢሮ ያሉ ነፍሳት የሰውኛ ባህሪ ሰጥተው ቀርፀዋቸዋል፡፡ እንደ ትዕምርት ደግሞ ‹‹ዛፍ›› ዘላለማዊ ህይወትንና ቤተሰብን፤ ‹‹ቢራቢሮ›› ነፍስን፤ ‹‹አበባ›› ውብ ልጃገረድን፤ ‹‹ወንበር›› ዙፋንን እንዲወክሉ ሆነው መቀረፃቸው የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

# ማውጫ


ምስጋና ..........

ማውጫ ..........

አጠቃሎ ..........

*ምዕራፍ አንድ*

1. መግቢያ ..........1

1.1. የጥናቱ ዳራ ..........1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..........1

1.3. የጥናቱ አላማ ..........3

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ ..........3

1.5. የጥናቱ ወሰን ..........4

1.6. የጥናቱ ዘዴ ..........4

*ምዕራፍ ሁለት*

2. ክለሳ ድርሳን ..........5

2.1. ንድፈ ሃሣባዊ ቅኝት ..........5

2.1.1. የአሊጎሪ ምንነት..........6

2.1.2. የአሊጎሪ ጠቀሜታ ..........9

2.1.3. አሊጎሪ በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ ..........12

2.2. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ..........15

*ምዕራፍ ሦስት*

3. አሊጎሪ በአማርኛ ዘመናዊ አጫጭር ልቦለዶች ..........19

3.1. አሊጎሪ በሰብሃት ገብረ እግዚአብሔር አጫጭር ልቦለዶች ..........33

3.1.1. ቢራቢሮ ..........34

3.1.1.1. አፅመ ታሪክ ..........34

3.1.1.2. ትንታኔ ..........35

3.1.2. አውራ ዶሮው ..........38

3.1.2.1. አፅመ ታሪክ..........38

3.1.2.2. ትንታኔ ....................................................................................40
3.2. አሊጎሪ በአዳም ረታ አጫጭር ልቦለዶች .................................................43
3.2.1. የአበቦች ታሪክ ......................................................................................44
3.2.1.1. አፅመ ታሪክ ..........................................................................44
3.2.1.2. ትንታኔ .....................................................................................46
3.2.2. የድንች መዋስዕት......................................................................................47
3.2.2.1. አፅመ ታሪክ .........................................................................47
3.2.2.2. ትንታኔ.........................................................................................49
3.3. አሊጎሪ በአማምነው ባረጋ አጭር ልቦለድ .............................................51
3.3.1. የአራዳው ወንበር........................................................................................51
3.3.1.1. አፅመ ታሪክ ..........................................................................52
3.3.1.2. ትንታኔ ....................................................................................53
3.4. አሊጎሪ በአለማየሁ ገበየሁ አጭር ልቦለድ ...............................................55
3.4.1. አስቸኳይ ጉባኤ ....................................................................................56
3.4.1.1. አፅመ ታሪክ ...........................................................................56
3.4.1.2. ትንታኔ .....................................................................................58
3.5 አሊጎሪ በሚካኤል ሺፈራው አጭር ልቦለድ ...............................................61
3.5.1. ሐረግና ግራር........................................................................................61
3.51.1. አፅመ ታሪክ ................................................................................61
3.5.1.2. ትንታኔ ........................................................................................63
ምእራፍ አራት፡- ማጠቃለያ ..........................................................................67
ዋቢ ጽሑፎች

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን እና የጥናቱ ዘዴ ተካተዋል፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

አሊጎሪያዊ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት ጥንታዊነት ያለውና የሰው ልጅን ሞራል ለማስተማርና በአብዛኛው ሃይማኖታዊ አስተምህሮን በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ለማስረፅ የሚሰራበት የአፃፃፍ ብልሃት ነው፡፡

አሊጎሪያዊ ሥነ ጽሑፍ የሰውን ልጅ ምግባሮች፣ ሞትና ህይወትን፣ ድንቁርና እና ዕውቀትን፣ ዕፅዋትንና አዝርዕትን፣ እንስሳና አራዊትን ሰናይና እኩይ ባህርያትን ሥጋ አላብሶ እንደሰው የማናገርን ሚና ይጫወታል፡፡ በተምሣሌታዊ እና በምፀታዊ አቀራረብ የሰውን ልጅ ባህርይ ለማቃናት ይረዳው ዘንድ እንስሳቱን፣ እፅዋቱን፣ አዝርዕቱንና ማንኛውንም ረቂቅ ባህርያት ይጠቀምባቸዋል፡፡ ስለዚህ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት በርካታ ምሁራን ሲያጠኑ ጥንታዊነቱንና ከሃይማኖታዊ አስተምህሮ ጋር እጅጉን የተቆራኘ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

አሊጎሪ÷ በተለያዩ አገራት የሚሰራበት ሲሆን፣ በአገራችንም 'ወዳጄ ልቤ' የተሰኘው የኅሩይ ወልደሥላሴ መጽሐፍ ጨምሮ፣ በተለያዩ ዘመናት በታተሙ መጻሕፍት፣ መጽሔቶችና ጋዜጦች ላይ አልፎ አልፎ ሲፃፍ ይስተዋላል፡፡

### 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማካሄድ ያነሳሳኝ ዋናው ምክንያት፣ በ2002 ዓ.ም፣ ክፍል ውስጥ በዘሪሁን አስፋው /ተ. ፕሮፌሰር/ አማካይነት፣ የ'prose fiction' ኮርስ በምወስድበት ጊዜ፣ በአሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት ስለተፃፉ ቀደምት አጫጭር ልቦለዶችና በዘመናችን ደግሞ በዚሁ ብልሃት ስለተጻፉ አጫጭር ልቦለዶች ሲያስተምሩ፣ 'ለምን

ትረካዎቹን ለይቼ ከአሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት አንፃር አላጠናቸውም?' የሚል ሃሣብ አድሮብኝ ነው፡፡

በዚህም የተነሳ ስለጉዳዩ ስሜት ሰጥቶኝ እከታተል ጀመር፡፡

በአስራ ዘጠኝ ሰላሳዎቹና አርባዎቹ በየጋዜጣው ይታተሙ የነበሩትን አጫጭር ልቦለዶች በምናይበት ጊዜ፣ በዘመኑ የነበሩ ደራስያን የትምህርትን አስፈላጊነት ለመግለጽ ዕውቀትን እና ድንቁርናን እንደ አሊጎሪ በመጠቀም ዕውቀትን መምረጥ ብልህነት እንደሆነ ያስረዱ ነበር፡፡ በፍርደ ገምድልነት የሚሰጥ ፍርድ ለሰማያዊም ሆነ ለምድራዊ ህይወት የማይበጅ መሆኑን ለማስተማር ደግሞ 'ፍትህ' እና 'እውነት' እንዲናገሩ በማድረግ የትውልዳቸውን ምግባር ለማረቅ እና ሞራል ለማነፅ ይጠቀሙበት እንደነበር፣ በዘሪሁን አስፋው የተሰናዳውን 'ልብወለድ አዋጅ እና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች ከቀደምት የኢትዮጵያ ደራስያን (1898-1948)› መጽሐፍ በማንበብ ለማወቅ ችያለሁ፡፡

በአሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት ስለተደረሱ ልቦለዶች ጥናት የመስራት ፍላጎቴ እየጨመረ ሲመጣ፣ ከዚህ ቀደም ያነበብኳቸውና ለአሊጎሪ የአፃፃፍ ብልሃት በቂ ምሣሌ ይሆናሉ ብዬ ያመንኩባቸውን የፈጠራ ሥራዎች እንደገና በማጤን፣ ስለ ሥነ ጽሑፍ ብልሃቱ የሚተርኩ የውጭ አገር መጻሕፍትን በማገላበጥና፣ መምህራንን በመጠየቅ ሃሣቡን አዳብረው ያዝኩ፡፡

በጉዳዩ ላይ ያለኝ ግንዛቤ እየሰፋ ሲመጣ፣ ርዕሰ ጉዳዩን መቀንበብና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተፃፉትን የአማርኛ አጫጭር ልቦለዶችን መከታተል ጀመርኩ፡፡ በዚህም የተነሣ ስብሃት ገ/እግዚአብሔር፣ አዳም ረታ፣ አሣምነው ባረጋ፣ አለማየሁ ገበየሁና ሚካኤል ሺፈራው በዚሁ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት ሊመደቡ የሚችሉ ልቦለዶችን ጽፈው በማግኘቴ በጉዳዩ ላይ ጥናቱን ለማድረግ በቂ ምክንያት ሆነኝ፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ አላማ የአሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት በአማርኛ ዘመናዊ አጫጭር ልቦለዶች ውስጥ ያለውን ሚና፣ በታሪክና በሐቲት ደረጃ ማሣወቅ እና የሥነ ጽሑፍ ብልሃቱ ምንነትና ጠቀሜታ ማሣየት ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ጥቅል ዓላማ በመነሣት ጥናቱ የሚከተሉት ንዑስ አላማዎች ይኖሩታል፡፡ እነሱም፡-

1. የሥነ ጽሑፍ ብልሃቱ ምንነትና አሊጎሪ ሥነ ጽሑፍ የሚታይበትን ባህርያት ማሳየት፣
2. የሥነ ጽሑፍ ብልሃቱ ፋይዳ ማሣየት፣
3. በሥነ ጽሑፍ ብልሃቱ ተጠቅመው ሥራዎቻቸውን ለንባብ ያበቁ ቀደምት የአማርኛ ደራስያንና ሥራዎቻቸውን ማስተዋወቅ፣
4. በሥነ ጽሑፍ ብልሃቱ በመጠቀም በአማርኛ ቋንቋ የተደረሱ ዘመናዊ አጫጭር ልቦለዶችን መተንተን፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

- የአሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት ምንነት፣ ጠቀሜታው እና በብልሃቱ ውስጥ ተዘውትረው የሚታዩ ባህርያትን በማስተዋወቅ በኩል ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡
- በአሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት ተጠቅመው ልዩ ልዩ አጫጭር ልቦለዶችን በአማርኛ ቋንቋ የደረሱ ኢትዮጵያውያን እና ለብልሃቱ መበልፀግ አስተዋጽኦ ያደረጉ ደራስያንን ያስተዋውቃል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ "አሊጎሪ በአማርኛ ዘመናዊ አጫጭር ልቦለዶች" የሚለው ጥናት ወሰን፣ በርዕሱ እንደተገለፀው በአማርኛ ቋንቋ የተፃፉትን አጫጭር ልቦለዶችን እንጂ በሌሎች ቋንቋ የተደረሱትን አይመለከትም።

በጥናቱ ውስጥ የሚካተቱት ዘመናዊ አጫጭር ልቦለዶች በመጽሐፍ መልክ ታትመው ለተደራሲያን የቀረቡትን እንጂ በሌሎች የህትመት ሚዲያዎች ማለትም በመጽሔትና በጋዜጣ ለንባብ የበቁትን አይዳስስም።

ምንም እንኳን በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ የአሊጎሪካዊ የሥነ ጽሑፍ ብልሃትን ተጠቅሞ ድርሰት መጻፍ ከበፊት ጀምሮ የነበረ ቢሆንም፣ የዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫ ግን፣ ዘመናዊ የአጭር ልቦለድ በኢትዮጵያ ውስጥ መጻፍ ከተጀመረ፣ (ከ1941 ዓ.ም ከታተመው ከተመስገን ገብሬ 'የጉለሌው ሠካራም' አጭር ልቦለድ በኋላ) ለሕትመት የበቁ ሥራዎች ብቻ መቃኘት ነው።

በዚህም መሠረት፣ በዚህ ጥናት ውስጥ በአምስት ደራስያን የተፃፉት ሰባት አጫጭር ልቦለዶች ይዳሰሳሉ። በስብሃት ገ/እግዚአብሔር ከተደረሰው *አምስት ስድስት ሰባት* መድበል ውስጥ የሚገኙት *ቢራቢሮ* እና *አውራ ዶሮው*፣ በአዳም ረታ ከተደረሱት ሁለት መጽሐፎች ማለትም *ከማኅሌት* መድበል ውስጥ *የአበቦች ታሪክ*፣ *ከአለንጋና ምስር መደበል* ውስጥ *የድንች መዋስዕት* የተሰኙትን፣ በአማምነው ባረጋ ከተደረሰው *የትሮይ ፈረስ* መድበል ውስጥ *የአራዳው ወንበር* የሚለውን፣ በሚካኤል ሺፈራው ከተደረሰው *የወፍ ማስፈራሪያ መድበል* ውስጥ *ሀረግና ግራር* የተሰኘውን እና በአለማየሁ ገበየሁ ከተደረሰው *የሀበሻ ፊት መድበል* ውስጥ *አስቸኳይ ጉባኤ* በሚል ርዕስ የቀረቡት ተካተዋል።

## 1.6. የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ የሚቀርብበት መንገድ ሥራዎቹን በመተንተን እና የትንተና (Analysis) ስልት በመከተል ይሆናል። ስለ አሊጎሪ የሥነጽሑፍ ብልሃት ምንነት የሚያስተዋውቁ መጻሕፍትን በማገላበጥ እና ስለ ብልሃቱ የተደረጉ ጥናቶች በመመርመር ይሆናል።

# ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳን

በዚህ የክለሳ ድርሳን (Literature Review) ክፍል ውስጥ የንድፈ ሃሳባዊ እና የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት እንዲሁም የአሊጎሪን ምንነትና ጠቀሜታን የሚያሳዩ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡ በመጀመሪያ የቀረበው ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝቱ ነው፡፡

## 2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

ሥነ ጽሑፍ ገሀዱን ዓለም አጢኖ፥ ያጤነውን ነገር በውበት ከይኖ በቃላት ከሽኖ ለአንባብያን የሚያቀርብ የፈጠራ ውጤት ነው፡፡ የገሀዱን ዓለም ህይወት ተንተርሶ ይቅረብ እንጂ፥ ሥነ ጽሑፍን ሥነ ጽሑፍ የሚያደርገው በታሪክ ከሚዘረዘረው የኑሮ ትግልና ዝባዝንኬ ባሻገር የአቀራረብ ብልሃቱ ነው (Amelia, 2007)፡፡ የሥነ ጽሑፍ ሰው ከሌላው የጽሑፍ አቅራቢ ማለትም ከሳይንስ፣ ከፖለቲካና ከሌሎች የሕብረተሰብ ሳይንስ ጽሑፍ አቅራቢዎች የሚለየው፤ ከተለምዶአዊና ኢ-ልቦለዳዊ ዘገባ በተለየ መልኩ ለጽሑፉ ኪናዊ ለዛ የሚጨነቅ በመሆኑ ነው፡፡ ‹ዝም ብለን፣ አንድ ቀን ወፈፍ ጨምደድ ያደረገን ዕለት ተነስተን እስቲ ወደ ገበያ ልውጣ እንደሚባለው፣ እስቲ ድርሰት ልፃፍ አይባልም› (ዮናስ፡ 2001)

የሥነ ጽሑፍ ሥራው ዘመናትን የመሻገር ዕድሉ እንዲሰፋ ደራሲው፤ በአጻጻፍ ብልሃቱ የረቀቀ ሊሆን እንደሚገባው ግልፅ ነው፡፡

> ሥነ-ጽሑፍ በቃል ጥበቡ ወይም በአጠቃላይ በድርሰት ብልሃቱ አንኳር የሕይወት ውጣ ውረዱን፣ በውበት ሞሽሮ ማራኪነትን፣ እንግዳነትን ለድርሰቱ አላብሶ ካላቀረበ ያው በተለምዶ ከሚደሰኮረው ከሚስፋፋው እንካስላንቲያ፣ ሹክሹክታና የነገር እንቶ ፈንቶ እንዴት ይለይ? እና ይህንን በማጤን መሰለኝ፤ ሥነ ጽሑፍ የሚተረከውን በብልሃት በማቅረቡ ላይ ትኩረት ሠጥተው የሥነ ጽሑፍ ጥበባዊነት በአቀራረብ ብልሃቱ ላይ ይወሰናል የሚሉት . . . /ሳሙኤል፡ 94/

የአቀራረብ ብልሃት ስንል ደግሞ፤ የታሪክ አደራደሩን፣ የገፀባህርይ አሳሳሉን፣ የድርጊት አሰናሰሉን፣ የቴክኒክ አመራረጡን፣ የቋንቋ አከያየኑን ያካትታል፡፡ ከአቀራረብ ብልሃቶች አንዱ ደግሞ አሊጎሪ ነው፡፡ (Baldic, 2001)

## 2.1.1. የአሊጎሪ ምንነት

አሊጎሪ የሚለው ቃል ከላቲን ቋንቋ የተገኘ እና ከሁለት ንዑስ ቃላት የተገነባ ነው:: ቃላቱም ኤሎስ Γαλλos (allos) እና ኢጎሪዮን áyopeúw (agoreuo) ናቸው፤ ኤሎስ ማለት ሌላ፡ የተለየ ማለት ሲሆን፤ አጎሪዮን ደግሞ መናገር ወይም መተረክ የሚለውን ፍቺ ይሰጣል:: ይህም በንግግር የቀረበ ታሪክ ወይም ትረካ ሌላ ሀሳብን እንዲያመለክት አድርጐ የማቅረቢያ መንገድ የሚለውን ቀጥተኛ እሳቤ ያመለክታል (Amelia, 2001):: ከቃሉ እንደምንረዳው አሊጎሪ፡ ከተባለው ሌላ ተጨማሪ ፍቺን ወይም ታሪክን ይይዛል፤ ሠምና ወርቅ በሆነ አቀራረብ ረቂቅ ባህርያትን ተውሶ የሚንቀሳቀሱ ገፀባህርያትን ይፈጥራል::

አሊጎሪ÷ አንድ ታሪክ ወይም ስዕል፤ ከሚታየው እና ከሚታወቀው ትርጉም ሌላ፤ ሁለተኛ እና ድብቅ ትርጓሜ የሚሰጥ ነው:: መሠረታዊው የአሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃ ሰውኛ ዘይቤን በማዘውተር የሚታወቅ ሲሆን፤ ረቂቅ ባህርያትን የሰው ባህርይና ቅርፅ ይሰጣቸዋል፤ ለምሣሌ እንደ ነፃነት ወይም ፍትህ ያሉ ረቂቅ ባህርያት:: አሊጎሪ ወደ ለዋጭ ዘይቤ እና ወደ ተለያዩ መዋቅሮች ሊሰፉ ይችላል:: ተፅፈው በምናገኛቸው አሊጎሪ ልቦለዶችም፤ ሁለት እና ከሁለት በላይ የሆኑ ትርጓሜዎችን በመስጠት ይታወቃል ይላሉ ሱቲ ፓውል::

> Allegory, a story or visual image with a second distinct meaning partially hidden behind its literal or visible meaning. The principal technique of allegory is a personification, when by abstract qualities are given human shape-as in public status of liberty or justice. An allegory may be conceived as a metaphor that is extended in to a structured system. In written narrative allegory involves a continuous parallel between two (or more) levels of meaning in a story, so that its persons and events external to the tale. (Suttie, 2006)

ምንም እንኳን ስለ አሊጎሪ ምንነት የተለያዩ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ምሁራን ትርጓሜ እና ትንታኔ ቢሰጡም፤ ቃሉን ወደአማርኛ ሲመልሱት አይታይም ዓለማየሁ ሞገስ ግን አሊጎሪን ከዘይቤ ዓይነት እንደ አንዱ ቆጥረው ትንታኔ

ከመስጠታቸው በተጨማሪም፣ አሊጎሪን ‹ጽላሎት› የሚል ፍቺ ይሰጡታል፡፡ ጽላሎት የግዕዝ ቃል ሲሆን ፍቺውም ጥላ ነው፡፡

> ምሳሌና ተረት አስመስሎ ጥልቅ ትምህርትን የሚሠጥ የንግግር ስልት ጽላሎት ይባላል፡፡ በዚህም የተሰየመበት ምክንያቱ ጥላ በግዙፍ ነገር አምሳያ እንደሆነች እሱም ለረቂቅ ምግባርና ሕልውና አምሳል መርገፍ ስለሆነ ነው፡፡ ለቅኔ ጀማሪ ከሰም ለበስ ጋራ ተመሣሣይ ይመስላል፣ ልዩነታቸው ግን ጸላሎት ዝርው እንደመሆኑ ግጡን አያኳሽም፣ ሰም ለበስ ግን ባያኳሽ ይፀድቅና ቅኔ መሆኑ ይቀርበታል፡፡ በአራት ወንጌል ጽያሔ ፍኖት /መንገድ ጠራጊ/ እየሆነ የተነገረው ሁሉ ጽላሎት ነው /ዓለማየሁ፡54/

ይህ በመንገድ ጠራጊነት የተመሰለው ጽላሎት /allegory/ ምሳሌና ተረት በሚሉ ስያሜዎችም ይጠሩታል፡፡ ይህንንም ከላይ የተጠቀሱት አጥኚ በምሳሌ ሲያስረዱ፣ አብርሃም ለኢየሩሳሌም ንጉሥ ለመልከ ጼዴቅ ያቀረበው ወይንና ስንዴ የሥጋው ወደሙ ምሳሌ መሆኑንና ድርጊቱም በክርስቶስ እንደሚመሰል፣ ጌታ በወንጌል ላይ በሚያስተምር ጊዜ በስብከቱ መሐል ብዙውን ጊዜ ምሳሌ ይጠቅስ እንደነበር፣ አባቶቻችን በጦጣ፣ በዝንጀሮ፣ በቀበሮ ወዘተ እየመሰሉ ሲናገሩት የኖሩት ተረቶች በዚህ ስያሜ ስር እንደሚጠሩ ያትታሉ፡፡ /ዓለማየሁ፡ 54/

ከላይ የተጠቀሰውን ፍቺ ተቀባይነት እንደሌለው የሚያትቱ አጥኚዎች ደግሞ አሊጎሪን እንደዘይቤ መቁጠር እንደማያስኬድ ሲያመለክቱም አሊጎሪና ዘይቤ ቃላዊ መዋቅር እንደሌላቸውና ከዘይቤ ይልቅ እንደ ፍቺ መንገድ፣ እንደትርጓሜ መንገድ መመልከት የተሻለ መሆኑን ይገልፃሉ ለዚህም ነው፣ በባህርይ ተመሳሳይነት ያላቸው ነገሮች የሚዛመዱበት፡፡ አንድን ነገር እንዲወክሉ የተመረጡ ሁለት ሃሳቦች እንደሚዛነቁበት፡፡ በትረካው ውስጥ ነገሮች፣ ሰዎች ወይም ድርጊቶች ተሰውኝተው ሌሎች ነገሮችን ወይም ሁነቶችን ወይም ድርጊቶችን እንዲያመለክቱ የሚደረግበት ጥበብ ከመሆኑም በተጨማሪ ትረካው ብዙ ባህርያት እንዳሉት አቶ ብርሃኑ ገበየሁ ይጠቅሳሉ፡፡

> አንደኛ፡- ግጥሙ አንድ ታሪክ ይነግራል፡፡ ስለዚህ ታሪክ የተመሰረተባቸውን ድርጊቶች የሚፈፅሙ ገጸሰቦች ወይም ገጸባህርያት ይኖራሉ፡፡

ሁለተኛ፡- በታሪክ ውስጥ የሚሳተፉት ገጸሰቦች ብዙውን ጊዜ አል-ሰዋዊ ናቸው፡፡ እንስሶች፣ ዕፅዋት፣ የተፈጥሮ ክስተቶች፣ ሰው ሰራሽ ቁሳቁስ ወይም አዕምሯዊ አርቅቶቶች ለምሳሌ ሃሳቦች፣ ስሜቶች /ፍቅር፣ ጥላቻ/፣ ሰብዐዊ ባህርያት /ተንኮል፣ ደግነት፣ እምነት፣ ክህደት/፣ ወዘተ፣ እሳቤዎች /እምነት፣ ማኅበራዊነት/፡፡ እነዚህን መሰሎቹ ነገሮች በገጸባህርያት ሲሳሉ ይወሰኛሉ፤ የሰውን ልጅ አካላዊና ባህርያዊ ችሎታዎች ይወስዳሉ፡፡ የአሊጎሪ ገፀባህርያትና እነርሱ የሚፈፅሙዋቸው ተግባራት፣ በመካከላቸው የሚኖረው ትስስር /ዝምድና ወይም ቅራኔ/ ለልዩ ልዩ ሰዋዊ ድርጊቶችና ሃሳቦች መወከል በመሆናቸው ትዕምርት /ምልክት/ ናቸው፡፡

ሦስተኛ፡- አሊጎሪያዊ ታሪክ ሁለት ፍቺዎች አሉት፡፡ አንደኛው ፍቺ የታሪክ ላዕላይ ፍቺ ወይም የዝርው ፍቺ ሲሆን ሁለተኛው አንባቢ በራሱ የሚደርስበት የአንድምታ ፍቺ ነው፡፡ በቀጥታ የሚነገረው ላዕላይ ፍቺ፣ ፋይዳቢስና ፍሬከርስኪ በመሆኑ በአሊጎሪያዊ ትረካ የግጥሙ ፍሬ ነገርና መልዕክት የሚነጥረው ከትርጓሜው ወይም በአንድምታ ፍቺው ነው፡፡

አራተኛ፤ አሊጎሪያዊ ትረካ የሚጨርሰው ደራሲው ለአንባቢ ሊነግር በሚሻው ሥነምግባራዊ አስተያየት ነው፡፡ ይህም ሥነምግባራዊ አስተያየት ትረካው የተመሠረተበትን እውነትና ሃሣብ ይገልጣል፡፡ በሌላ አባባል አሊጎሪያዊ ትረካ ራሱን ይተረጉማል፤ ይፈታል /ብርሃኑ፡99/

ከላይ እንደተጠቀሰው ፍቺው ጥልቅና ከሌሎች የዘይቤ ዓይነቶች የመመሳሰል፤ እርስ በርስ የመዋኻድ ባህርይ ይታይበታል፡፡ አመዛኙ ሰውኛ ዘይቤን ይጠቀማል፡፡ ምንም እንኳን አንድን ነገር በሌላ መስሎ በማቅረቡ ምሰላን ዘይቤን የመምሰል ባህርይ ቢኖረውም፤ ምንም እንኳን እንስሳትን ዕፅዋትንም በሰውኛ ዘይቤ አነጋግሮ መልዕክት የማስተላለፉን ዘዴ ቢጠቀምበትም አሊጎሪ ረቂቅ ባሕርያትን ማለትም እንደ ፍትህ፣ ዕውቀት፣ ሠላምና ጦርነትን፣ እኩይና ሠናይ ባሕርያትን በመወከል ይታወቃል፡፡

በአጠቃላይ አሊጎሪ ሰውኛ ገጸ ባህርያትን ከመጠቀም ባሻገር ትዕምርቶችን፣ ምልክቶችንና የሚፈከሩ ልቦለዶችን በማስገባት ከተነገረው ነገር ሌላ ያልተነገረ ነገር የምናወጣበት የሥነ ጽሑፍ ብልሃት ነው፡፡

### 2.1.2. የአሊጎሪ ጠቀሜታ

በአሊጎሪ ድርሰት ውስጥ የምናገኛቸው ረቂቅ ባህርያት ወይም አራዊትና እንስሳት ወይም ግዑዛን እንደሰው የመከራን ድልድይ መሻገር አቅቷቸው ተሰናክለው ሲወድቁ፣ እንደ ሰው የድል አክሊልን ተጎናፅፈው ወደ አደባባይ ሲዘልቁ፣ እንደ ሰው በመኖር እና በመሞት መካከል ባሉ ፈተናዎች ሲንገላቱ ከማሳየታቸውም በላይ ዋነኛ ጠቀሜታቸው የሰው ልጅ በሥነ ምግባር የታነፀ እንዲሆን ማስቻል እና ለማኅበረሰቡ ደንብ ተገዝቶ ነባር የሆኑ ሠናይ ምግባራት አጽንቶ እንዲቆይ የሚያደርገው የጥበብ ሙዳይ ነው፡፡

በአሊጎሪ የአፃፃፍ ብልሃት ውስጥ እያንዳንዱ ነገር በሌሎች ነገሮች ተመስሎ፣ ሃይማኖታዊ፣ ሞራላዊ፣ ምግባራዊና ፖለቲካዊ መልዕክቶችን ያስተላልፋል፡፡ ትረካው በልዩ ልዩ ምልክቶች (signs)፣ ትዕምርቶች (symbols) ወይም ተደጋግመው በሚጠቀሱ ምስሎችና ሀተታ ተፈጥሮ (myth) በመጠቀምም ጽሑፉን በጭብጥና ከውበት ዘርፍ ያበለፅገዋል፡፡ እነዚህ ምልክቶች፣ ትዕምርቶች እና ምስሎች ያለ አንዳች አገልግሎት ትረካው ውስጥ አይከሰቱም፡፡ ትረካው በእነዚህ አማካይነት የሰውን ልጅ ባህርይ ያቃናል፤ ጎባጣ መስሎ የታየው መንገድ ያቀናል፡፡ በርግጥ የአንድ ማኅበረሰብ አኗኗር ለመሄስ የተጻፈ 'አሊጎሪ'፤ በውስጡ የተገለፁ ተምሳሌቶች ለሌላው ማኅበረሰብ ባዕድ የሚሆኑባቸው አጋጣሚዎች አሉ፡፡

የአሊጎሪ ትረካ አንዱ ጥቅም ትረካውን ከታሪክ ጋር አዛምደንና አዛንቀን ትርጓሜ እንድናበጅ ያደርገናል፡፡ ለዚህ ምሳሌ ይሆነን ዘንድ፣ በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ ሰባት ላየ የሰፈረውንና ናቡከደነጾር ያየውን ህልም ማየት እንችላለን፡፡ ‹... እነሆ ነብር የምትመስል በጀርባዋ ላይ አራት የወፍ ክንፎች የነበሩአት ሌላ አውሬ አየሁ፤ ለአውሬይቱም አራት ራሶች ነበሩአት÷ ግዛትም ተሰጣት...›

ይህንን አንቀፅ አንዳንድ የሃይማኖት ተቋማት የሚከተለውን ፍቺ ይሰጡታል፡፡ በትንቢቱ ላይ የተገለፀው ቁጥር አራቱን መንግስታት ለማመላከት ነው፤ ፖርቹጋል፣ ስፔን፣ እንግሊዝና ፈረንሣይን፡፡ የእነዚህ አገራት በአውሬይቱ በነብር መመሰልስ?! ... ጥቂቱን ልጥቀስ

- በነብር ቆዳ ላይ ሁለት ቀለሞች ተዥጐርጉረው እንደሚታዩ እንዲሁ ጥቁሩን ሕዝብ ከአፍሪካ ነጩን ከአውሮፓ ውሰደው በአሜሪካ ምድር ቆዳ ላይ አዥጐርጉረውት መታየታቸው፡፡
- የነብር ቀለም በአንድ ቆዳው ላይ እንደሚለያይ እነዚህም አገሮች በአንድ ዓላማ ላይ መለያየታቸው፡፡ ነብር አዳኙን ይዞ ጓደኛው እንዳይበላበት ቢነፋ፣ ቢቀትት፣ ቢያጉረመርም ብርቱ ጓደኛው ነጥቆ እንደሚበላበት እንዲሁም እነዚህ አገሮች በዘረፉቸው ላይ አንዱ የሌላውን እንዳይነካበት ሕግ ቢደነግግም (አደኑን ይዞ ቢያጉረመርም) መዘራረፍ መቀማትም ብሎም መዋጋት አልቀረም፡፡
- ነብር የግዳዩን ደም ይመጥጣል፤ ሥጋውንም አበስብሶ አትልቶ ይበላል፡፡ ባሪያ ገዥዎችም ገርፈው አቆሳስለው ሥጋውን ጉልበቱን በሉ፤ ደሙንም መጠጡ፡፡
- በጥቂቱ በዘረዘርኳቸው ዋና ዋና ምክንያቶች ፖርቹጋል÷ ስፔን÷ እንግሊዝና ፈረንሳይን ያቀፈች ሦስተኛዋ የአውሮፓ መንግስት ‹‹ነብር ትመስል ነበር›› ተባለች፡፡ (ያየህ ይራድ፡ 2000 ዓ.ም)

የአሊጐሪ አፃፃፍ ዘዴ ጥንታዊ ነው፡፡ በጥንታውያኑ በሆሜር ድርሰቶች ውስጥ አሊጐሪያዊ ባህርያትን በሚያሟሉ ልቦለዶች እናነባለን፤ በብሉይ ኪዳን ውስጥም እናገኛለን፡፡ የጥንት ሃይማኖተኞች ደግሞ፤ የግሪክን ሐተታ አማልክት መነሻ በማድረግ ለዐውደ ከዋክብት (astrologic allegories) ተጠቅመውባቸዋል፡፡ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የምናገኛቸው አንዳንድ ልቦለዶች ትንቢቶች ናቸው፤ ስለክርስቶስ አመጣጥና ባህርይ የሚተርኩ፡፡ የአሊጐሪ አፃፃፍ ዘዴ እና ታሪካዊ አንድምታዎች የሚመሳሰሉባቸው ብልሃቶች እንዳሉ ለማጠየቅም ትላንት የተፃፈው ነገር ለዛሬ ሁነት ተስማምቶ ወንጌል ሲሰብክ '...እንደተነገረው፣ ...እንደተፃፈው፣ . . . እንዲል መጽሐፉ' በማለት፣ የብሉይ ነቢያት የፃፉዋቸውን ዐርፍተ ሃሳቦች መዝዞ፤ ከአሁን ድርጊት ጋር አያይዞ እየተባለ ያለው ነገር ሁሉ አዲስ እንዳልሆነ ያስረዳበት መንገድ እንደ አሊጐሪ እንደሚጠቀስና የዘዴውን ነባርነት ማሣያ ምሳሌ መሆኑ ይነገራል፡፡ (Rose, 2005)

የተራራው ስብከት በመባል የሚታወቀው እና በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ላይ የሚገኘውን የኢየሱስ ክርስቶስ እዚህ ላይ ለምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

‹‹ምሳሌውን ከበለስ ተማሩ ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠሏም ሲያቆጠቁጥ ያን ጊዜ በጋ እንደቀረበ ታውቃላችሁ፤ እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ ስታዩ በደጅ እንደቀረበ

እወቁ›› የሚለውን የወንጌል ቃል አንድ ሃይማኖታዊ መጽሐፍ እንደሚከተለው ትንታኔ ይሰጥበታል፡፡

> በበለስ ዛፍ የተመሰለችው እስራኤል ናት፣ አያጠያይቅም፡፡ የበለስ ዛፍ ዛፍም የመጨረሻው የእስራኤል ትውልድ ሲሆን፣ አይሁድ በተለያዩ ጊዜዎች ረግፈውና ወደየሀገሪቱ ተበትነው ሕዝቧንና መንግስት አልባ የነበረችው እስራኤልም ቅጠሏ ረግፎ ራቁቷን በነበረች በበለስ ዛፍ ተመለሰች፡፡
>
> የበለስ ዛፍ መለስለስ፡- በዝርወት ይኖሩ የነበሩ አይሁድ የመጨረሻው ትውልድ ኅብረት የጽዮናዊያን ምክር ቤት መቋቋም፣ የቅጠልዋም ማቆጥቆጥ፣ ወደሀገራቸውም መሰብሰብና አሁን ያለውን የመጨረሻ መንግስታቸውን መቋቋም የሚያመለክት ነው፡፡ (ያየህ ይራድ፣ 2000 ዓ.ም)

አሊጎሪ በአራት ይከፈላል፡፡ እነሱም ታሪካዊ፣ መንፈሳዊ፣ ምግባራዊና ፖለቲካዊ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በመካከለኛው ዘመን ዕውቅና ያተረፈው የአሊጎሪ ባህርይ የታየበት ሥራ ማንም ሰው /every man/ የተሰኘው ቴአትር ሞራልን ለመስበክ የተፃፈ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በመካከለኛው ዘመን የአሊጎሪ ድርሰቶች መነሻቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ እና የሥነ ጽሑፍ ውጤቷ መተወኛ መድረክ ቤተክርስቲያን ነበር፡፡ ቀስ በቀስ ግን የአሊጎሪ አቀራረብ ዘዴ ከቤተክርስቲያን ደጅ ብቻ ሳይሆን ህዝብ በተሰበሰበበት መድረክ የሚታይ ሆነ፡፡ ሃይማኖታዊ ግጥሞች፣ ሃይማኖታዊ ድርሰቶችና ሃይማኖታዊ ተውኔቶች እጅጉን የተስፋፉበት ዘመን ነበር፡፡ ሃሳቦች እንደ ሰው ግዘፍ ነስተው የመንቀሳቀሳቸው ነገር ተቀባይነት እያገኘ በመምጣቱም 'Every man'፣ በእንግሊዞች ዘንድ እጅግ በጣም ምርጥ የሞራል መጽሐፍ የሚል ክብር ለማግኘት በቅቷል፡፡ ምንም እንኳን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያሉ ዘመነኛ ደራስያን አሊጎሪን እንደ አንድ የመልዕክት ማስተላለፊያ መልዕክት እየተጠቀሙበት ያለ ቢሆንም፣ ሲዘወተር እንደምናየው አሊጎሪ አብዛኛውን ጊዜ ሥነ ምግባራዊና መንፈሳዊ አስተሳሰቦችን ለማንፀባረቅ በሚፃፉ ሥራዎች ላይ የሚታይ ለመሆኑ የሚካድ አይደለም፡፡ (Suttie, 2006)

ለምሳሌ በጆርጅ ኦርዌል የተፃፈው የእንስሳት ዕድር/animal farm/ በገገሮችና በተገገሮች መካከል ያለ ሽኩቻን ይተርካል፡፡ ትረካው በፖለቲካዊ ምፀት የተሞላ አሊጎሪያዊ ሥራ ነው፡፡ የሰውን ልጅ በእንስሳ መስሎ ነው፣ ሰው በዚህ ዓለም ላይ

ሲኖር የተሻለ ሆኖ ለመገኘት የሚያደርገውን ተጋድሎ እየተሳለቀ የሚያቀርበው፡፡ ደራሲው ልቦለዱን የተሳካ ለማድረግ ሰውኛ ዘይቤን፣ ተላልቆንና አሊጎሪን ተጠቅሟል፡፡ በልቦለዱ ውስጥ የተጠቀሱት ገፀባህርያት እንደ ሰው ይናገራሉ እንደ ሰው ውስጣቸው ይታወካል፤ መንፈሳቸው በቁጣ ይሞላል፤ ሣቅና ፈገግታቸው፣ ልቅሶና ሀዘናቸው ከእንስሳት የማይጠበቅና ለሰው ልጅ ብቻ የተሰጠ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ዓሣማ ሣር ይነጫል እንጂ እንደ ሰብዐዊ ፍጡር ሥጋ የመጋጥ የአመጋገብ ስርዐት የለውም፡፡ (Orwell, 1945)

ኦርዌል፤ ልቦለዱን ለመፃፍ አሊጎሪን ስለተጠቀመ፤ የታሪኩ ፍሰት ለዛ ተላብሶ ፈገግታን አስጭሮ ጥልቅ የሆነ መልዕክቱን አስተላልፎበታል፡፡ ፍርደ ገምድሎችን ኮንኖበታል፡፡ በአሊጎሪ ትረካው ከትላንት ታሪክ እስከ መፃኢው ዘመን ሊሻገር የሚችል ትንቢት ተናግሮበታል፡፡ አብዮትን ገልጾበታል፤ ይህ ደግሞ ከሦስት መቶ ዓመታት በፊት ጀምሮ የዓለማችን ፖለቲከኞች አጀንዳ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡

## 2.1.4. አሊጎሪ በአማርኛ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ

በኢትዮጵያ ባህልና ትምህርት ‹አንድምታ› ተብሎ የሚጠራው ትርጓሜ ከአሊጎሪ ጋር የሚዛመድበት ባሕርይ አለው፡፡ ‹አንድምታ›፤ በሊቃውንት ዘንድ አንዱን ቃል ወይም ዐረፍተ ነገር ከአንድ ጊዜ በላይ ሁለተኛ ሦስተኛ በማለት ፈንታ አንድም እያሉ እስከ ዐሥራ ሦስት ጊዜ በላይ ሊተረጎሙ እንደሚችሉ አንዳንድ አጥኚዎች ይናገራሉ፡፡ (ሠይፈ ሥላሴ፡ 2011)

ለምሳሌነቱ ከሚጠቀሱት መሃል፤ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፤ መንግስተ ሰማይ በተለያዩ ምዕራፎች በተለያየ መንገድ ስትገለፅ ይነበባል፤ በመልካም ዘር፣ በሰናፍጭ ቅንጣት፣ በእርሾ፣ በተሰወረ መዝገብ፣ እንቁ በሚሻ ነጋዴና በመረብ፡፡

> የአንድምታ ትርጉም እንደ ኢትዮጵያ ባህል ፊደላዊ ሳይሆን ምሥጢራዊ ነው፡፡ ማንኛውም የቅዱሳት መጻሕፍት ንባብ ወይም ቃል ከፊደላዊ ትርጉም በስተኋላ ምስጢራዊ ወይም መንፈሳዊ ትርጉም ስላለው ይህ የተደበቀ ምስጢር መገለጥ እንዳለበት በማመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መምህራን ማንኛውንም ንባብ በአንድምታ ለመተርጎም ይሞክራሉ፡፡

‹‹እስመ ንባብ ይቀትል ወትርጓሜ የሐዩ፣ ንባብ ይገድላል ትርጓሜ ግን ያድናል›› (2 ቆሮ 3-6) እንደተባለው የቅዱሳት መጻሕፍት ንባብ በአንድምታ ምስጢር ካልተተረጐመ እልፍ እልፍ አስቸጋሪ ንባብ ሊኖር ይችላል (ሠይፈ ሥላሴ፡ 2011)

ይህ የአንድምታ አተረጓጐም በባህርይው አሊጐሪ ሚሟላት ከሚገባቸው ነገሮች ዋናውን ይዟል፡፡ ይህም የተደበቀ ምስጢርን ለመግለጥ የሚደረገው ምርምር ነው፡፡ አንድምታ ልክ እንደ አሊጐሪ ከተነገረው ነገር በስተጀርባ ሌላ መልእክት ይዞ ይመጣል፡፡ አንዱን ነገር በሌላ ነገር መስሎ በማቅረቡም፣ ምንም እንኳን አሊጐሪ የሚለው ቃል በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ባህልና ትምህርት የሚዘወተር ቃል ባይሆንም፣ የትርጓሜ መንገዱ ግን ጥንታዊ ነው፡፡

ልክ እንደሌሎች አገራት ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን ለማስተላለፍ ስንጠቀምበት ቆይተናል፣ ነባር የሀበሻ ልማዶች እንደይጣሱ እና እንዳይጣረሱ ሥነ ምግባራዊ መልዕክቶችን ማስተላለፊያ በመሆን አገልግሏል፡፡ ‹… ባለፈው ጊዜ የሕግ አንቀጾች ሆነው በያደባባዩ ሲሰራባቸው ቆይተዋል› (ማኅተመ ስላሴ፥ 61)

ልቦለድና ሌሎች የፈጠራ ሥራዎች መታተም ከጀመሩ በኋላ፣ ቀደምት ጸሐፍት በግጥሞቻቸው፣ በተውኔቶቻቸው በአጫጭር ትረካዎቻቸው እና በልቦለዶቻቸው ነበረ፣ ነገራቸውን በምሳሌ ያቀርቡ የነበሩት፡፡ ለምሳሌ ያህል ሰውና እውቀት የተሰኘው መጽሐፍ መግቢያ ላይ ‹… ሰው እውቀትን አግኝቶ ቶሎ ለመክበር መፈለጉንና መጣጣሩን ስለምታመለክትና እውቀትም በአንዲት ቆንጆ ውብ በሆነች ሴት ተመስላ የምትገኝበትን› እንደምታስተዋውቀው ተገልጿል፡፡ (እምሩ፥ 48)

ለዚህም ነው አሊጐሪያዊ የአፃፃፍ ብልሃት፣ ኢትዮጵያውያን ከፈረንጅ የቀዱት ነው፣ ከዮሐንስ ቡንያን የወሰዱት ነው የሚለውን የቶማስ ኬንን ሃሣብ ብዙዎች ውድቅ የሚያደርጉት፡፡ ቶማስ÷ የኅሩይ ወ/ሥላሴን ‹ወዳጄ ልቤ› የተሰኘውን ልቦለድ ከዮሐንስ ‹የመናኝ ጉዞ› ጋር በማመሳሰል፣ ኅሩይ ተፅዕኖ አድሮባቸዋል ቢልም የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ አጥኚዎች ግን ይህንን ሐሳብ እጅጉን ይቃወሙታል፡፡

ከ‹ወዳጄ ልቤ› መጽሐፍ ቀደም ብሎ፣ ለንባብ የበቁ አንዳንድ ድርሰቶችም አሊጐሪያዊ የአቀራረብ ብልሃት ለኢትዮጵያ አዲስ አለመሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ በ1926 ዓ.ም በመክብብ ደስታ ተፅፎ የታተመው ያቶ መሰንበት

ባልንጀርነት ታሪክና የምስጋና ግጥም መጽሐፍ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን እነዚህ ሥራዎች የ‹ወዳጄ ልቤን› ያህል የአሊጎሪን ባህርያት በምልዐትና በስፋት ያካተቱ አይደሉም፡፡

ዮናስ አድማሱ÷ ‹ትሑታት ፋና አብሪዎች› ከሚላቸው ደራስያን አንዱ የሆኑትን ኅሩይ ወልደሥላሴን ‹... ከሀገሪቱ ባህል የሚያስፈልገው፡ ለሀገሪቱ ዕድገትና ብልጽግና እንቅፋት የሚሆነው ቀስ ብሎ፡ ቀፎው እንዳለ ሳይረበሽ በብልሃት እየተነቀሰ› እንዲወጣ ያደረጉትን አስተዋፅኦ፣ ‹ወዳጄ ልቤ›ንና ‹የልብ ሃሣብ›ን በመጥቀስ አክብሮታቸውን ይገልፃሉ፡፡ (ዮናስ፡ 2001)

ኅሩይ በመጽሐፎቻቸው መግቢያ ላይም ይህን የአሊጎሪ አቀራረብ እጅጉን እንደሚያስደስታቸውና መልዕክቶቻቸው ግባቸውን እንዲመታ እንደሚጠቀሙበት ያሣዩናል፡፡

> ‹... ጠጅ በብርሌ ነገር በምሳሌ እንደተባለ፣ ነገር ሁሉ በምሳሌ ሲሆን ለሰሚው በቶሎ ያስረዳዋል፡፡ ለገበሬ በእርሻና በእንጀራ፣ በወጥና በጠላ መስለው ከሚነግሩት እርሱ በሚያውቀው በእርሻ በዘር፣ በመከርና በበልግ መስለው ቢነግሩት ያስረዳዋል፡፡› (ኅሩይ፡ 1923)

> ‹... ደራሲም ድርሰት እየደረሰ መጽሐፍ ሲፅፍ፣ ከመላእክትና ከሰው ከእንስሳትና ከአራዊት ከአዕዋፍና ከተንቀሳቃሽ፣ ከተረትና ከጫወታ ከደስታና ከሐዘን ከሌላውንም ይህን ከመሰለ ሁሉ ምሳሌ እያመጣና እየጨመረ መጻፉ ለአንባቢው እንዳይሰለቸውና ለሰሚው እንዲገባው ነው እንጂ ሌላ ምክንያት የለበትም፡፡› (ኅሩይ፡ 1925)

የኅሩይ አሊጎሪያዊ አቀራረብ በነዮናስ አድማሱ እና በነአስፋው ዳምጤ ዘንድ ‹... የሚለወጠው እንዲለወጥ፣ የሚወገደው እንዲወገድ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን› ለማቀንቀንና ‹ግለሰብንም ሆነ ኅብረተሰብን ለመምከር ለማስተማርና ለማሻሻል› እንደተፃፉ (አስፋው፡ 2001) በጥናቶቻቸው ቢጠቁሙም፣ አያልነህ ሙላቱ ግን ከነሱ በተለየ መንገድ አሊጎሪያዊ አቀራረባቸውንና የፈጠራ ሥራዎቻቸውን ሥብጥ እጅጉን ይኮንናል፡፡ ‹... መጽሐፉ ቀዝቃዛና ፍዝ የሆኑ ተረቶችን ከመያዙም ባሻገር ከባድ የሃይማኖት ተጽእኖ አለበት...› በማለት (አያልነህ፡78)

ከቀደምት ደራስያን አንዱ የሆኑት ዮፍታሄ ንጉሴም፣ ‹አፋጀሺኝ› የተሰኘ ተውኔታቸው አቀራረብ አሊጎሪያዊ ነው፡፡

በዚህ አሊጎሪያዊ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት ተፅፈዋል ከሚባሉት መጻሕፍት አንዱ ‹ተረት ተረት የመሠረት› የተሰኘው የሀዲስ አለማየሁ መጽሐፍ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ 16 ተረቶችን የያዘ ሲሆን፣ ተረቶቹ ሙሉ ለሙሉ አዳዲስና በደራሲው የተፈጠሩ ናቸው፡፡ ደራሲው በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ‹... መልካም ተረት ሞራሉ ወይም አሳቡ ትምህርት የሚሠጥና ምሳሌውም ደስ እያለ የሚነበብና ተናፋቂ መሆን ይገባዋል...› የሚል ዐረፍተ ነገር ከማስፈራቸውም በተጨማሪ፣ ‹ጥጋብ ስስትን ያገባ እንደሆነ ረሃብን ይወልዳል› የሚለውን ተረት እንዴት እና ለምን ጉዳይ እንደፃፉት ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡ ደራሲው ለተባበሩት መንግሥታት ማኅበር ተጠባባቂ ኮሚቴ ተካፋይ እንዲሆኑ ተጋብዘው በሔዱበት ኢንተርናሽናል ሀውስ የተባለ ኒውዮርክ የሚገኝ፣ የኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ያቋቋሙት ማኅበር ተጋብዘው ያቀረቡት ጽሁፍ ነው፡፡ ደራሲው እንደገለጹት ‹... እንደሌሎቹ መልዕክተኞች ሁ፣ ጋብዞኝ በመጀመሪያ ስለ ኢትዮጵያ፣ ከዚያ በኋላ ስለ ቅኝ ሀገር አስተዳደር እንድናገር ስለጠየቀኝ፣ በኢትዮጵያ ላይ ከተናገርኩ በኋላ ስለ ቅኝ ሀገር አስተዳደር ይህን በድመትና በአይጥ የተመሰለ ተረት ተናገርሁ› ይላሉ፡፡

በአማርኛ ሥነ ግጥም ባህል አሊጎሪ የተዘወተረ የአፃጻፍ ቅጥ ነው፡፡ የአሊጎሪ ባህርያትን በመጠቀም ግጥም ከሚደርሱ እምር ገጣሚያን መካከል ከበደ ሚካኤል አንዱ ናቸው፡፡ (ብርሃኑ፡ 99)[A]

በተሻገር ውቤ የተደረሰው ‹አቤቱታ› የተሰኘው ተውኔት አማርኛ፣ እንግሊዝኛ ጣሊያንኛን ፈረንሣይኛን የሚያናግር አሊጎሪ ድርሰት ሲሆን፣[B] በገብረ ኢየሱስ ኃ/ማርያም ‹የአካላት ሴራ› ደግሞ፣ ዓይን፣ አፍንጫ፣ አፍ እና ሌሎች አካላት ተገንጥሎ ስለመኖር የሚያወጉበት እና የሚሟገቱበት፣ ፖለቲካዊ የሆነ አሊጎሪ ነው፣ በ1984 ዓ.ም የተፃፈ፡፡ በ2002 ዓ.ም የታተመው የአጥናፍሰገድ ይልማ ‹የእንስሳት ዐመፅና ድርድር› መጽሐፍም፣ አቀራረቡ ተውኔታዊና በግጥም የተሰናዳ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ተደርጎ ስለነበረው ስለ 1997 ዓ.ም ምርጫ፣ በአራዊትና በእንስሳት

መስሎ በዚያን ዘመን መንግስትን በሚደግፉና በሚቃወሙ ፓርቲዎች የሚሳለቅ ነው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ ማለትም የኢትዮጵያ ተውኔት፣ ልብወለድና አጫጭር ትረካዎች መዘመን ከጀመሩ፣ ከ1950ዎቹ ወዲህ አሊጎሪን እንደ አንድ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት ተጠቅመው የሚጽፉ ደራስያንን በብዛት ባናገኝም፣ አንዳንድ ደራስያን ግን ሃይማኖታዊ፣ ሞራላዊ፣ ምግባራዊና ፖለቲካዊ አሊጎሪ ድርሰቶችን ለንባብ አብቅተዋል፡፡

የዚህ ጥናት ዓቢይ ትኩረት እነዚህን አጫጭር ልቦለዶች አሊጎሪያዊ ባህርይ ተንትኖ ማቅረብ ስለሆነ፣ ትረካዎቹ በዚህ ክፍል መጥቀስ አስፈላጊ ስላልሆነ በቀጣይ ምዕራፍ ይዳሰሳሉ፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

በአገራችን በአሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት ላይ ብቻ በማተኮር የተፃፉ ጥናቶች በርከት ያሉ ባይሆኑም፣ ስለምንነቱ ትርጓሜ ለመስጠት የሞከሩ እና ምሳሌ ጠቅሰው ለማስረዳት የጣሩ ጥቂት አጥኚዎች አሉ፡፡ ከነዚህም መሃል የሳሙኤል አዳል 'ወዳጅ ልቤና አሊጎሪያዊ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት' እና የጌቴ ገላዬ ‹አሊጎሪና ተምሳሌት በአማርኛ ልቦለዶች ውስጥ' የተሰኙ ጥናቶች ተጠቃሽ ናቸው›፡፡

ሳሙኤል፣ የአሊጎሪን ምንነት በማስረዳት ጥናቱን ሲጀምር፣ አሊጎሪ የገሀዱን አለም የሰዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከረቂቅ ሃሣቦች ድርጊትና እንቅስቃሴ ጋር በማነፃፀር የሌላ ተራዛሚ ሀሳብ ማንፀሪያ ሆኖ እንደሚቀርብና ገፀ ባህርያቱ ሰው የሚፈፅመውን በመፈፀም የሰውኛ ዘይቤን መንገድ እንደሚከተሉ አብራርቷል፡፡ ረቂቁ ታሪክ ሁልጊዜም ተፈጥሮአዊ የሆነ ይዘት ይዞ የሚቀርበው ከቅዱሳት ታሪክና ከታሪክ መዛግብት እንዲሁም ትውፊታዊ ከሆኑ የሥነ ቃል ሀብቶች በመውሰድ መሆኑም በጥናቱ ተጠቁሟል፡፡

ወደ አገራችን ሥነ ጽሑፍ በመግባትም እንደ አሊጎሪ የሚጠቀሰውን የብላቴን ጌታ የኅሩይ ወ/ሥላሴ 'ወዳጅ ልቤ'ን ያነሳል፡፡

‹ወዳጄ ልቤ› ዕድሜው 18 ዓመት የሆነ አንድ ወጣት ከሠናይና ከእኩይ ባህርያት ጋር የሚያደርገውን ውጣ ውረድ ያሳያል፡፡ ወጣቱ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ ከደቡብ እስከ ሰሜን ይጓዛል፡፡ አጥኚው÷ ደራሲው ቀደም ሲል በመግቢያቸው የሰጡትን መነሻ አድርገው እንዳብራሩት ምስራቅ ወንጌልን፣ ምዕራብ የብሉያትን፣ ሰሜን የሊቃውንትን፣ ደቡብ የአዋልድ መጻሕፍትን ለማመልከት መሆኑ እና በመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕራፎች ባሉት የታሪክ አውድ ውስጥ ከሦስቱ ታላላቅ ዛፎች ጋር የሚገናኘው ወጣት የሥላሴን አንድም ሦስትነት ለማሣየት መሆኑን ያብራራል፡፡ መጽሐፉ መንፈሳዊና ምግባራዊ ይዘት ባላቸው አሊጎሪያዊ የአቀራረብ ብልሃቶች የተሞላ ቢሆንም ክርስቲያናዊ አመለካከትን በአንባቢው ዘንድ ለማስረፅ ታስቦ እንደሆነም ይገልፃል፡፡

ጥናቱ የመጽሐፉ ዋና ገፀባህርያት የሆኑትን *ትህትና፣ ድንቁርና* እና *ዕብሪት* እንዴት ተደርገው እንደተቀረፁ ያትታል፡፡ በ‹ወዳጄ ልቤ› ውስጥ አብዛኛው ገፀ ባህርያት እኩይ ባህርያትን ወክለው ቢቀርቡም እንደ ብላታ ቸርነት ያሉ ሠናይ ባህርያትም ስማቸውን የመሰለ ድርጊት ሲፈፅሙ እናያለን፤ በእነዚህ ገጸባህርያት አማካይነት *ሥነምግባራዊ* ጉዳዮችን ጥበባዊ በሆነ መንገድና በማራኪ አቀራረብ ለመጠቀም ብልሃቱን እንደመረጡት ጥናቱ ያስረዳል፡፡

በልቦለዱ ውስጥ የፍቅር ጠላት ሆነው የተሣሉት *ሹመት፣ ጉቦና ሀሜት* መሆናቸውን፤ ሰዎች በ*ሹመት* የሚያኙትን ስልጣን በአግባቡ ካልተጠቀሙበት ለሠው ልጅ ያላቸው ፍቅር እየጠፋ ሰውን ለመጉዳት እንደሚሰማሩ፤ ሹመትን ለግል ምኞትና ለግል መጠቀሚያነት ማዋል ምግባራዊ ዝቅጠትን እንደሚያስከትል የሚጠቁም *ሥራ* መሆኑን ምሣሌ እየጠቀሰ ያብራራል፡፡

ከአሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት አንፃር ‹ወዳጄ ልቤ› ውስጥ ጎልተው የወጡ ድክመቶችን አጥኚው ሲያስረዳም፤ መጽሐፍ ቅዱስን በማጣቀስ የቀረቡ ጥቅሶች የቀረቡባቸው የማንፀሪያ መንገዶች ከመንፈሳዊ መልዕክቱ ያፈነገጠ መሆኑን ምሣሌ ጠቅሶ ያስረዳል፡፡

እንደ ሳሙኤል ጥናት፣ የ‹ወዳጄ ልቤ› ደራሲ 'ክብሩህ ተስፋ ይልቅ የአለምን ከንቱነት ወደ መስበክ' እንደሚያደሉ ያትታል፡፡

ምንም እንኳን ይህ ጥናት÷ በአሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት ላይ ትኩረት አድርጎ፣ የጥናቱን ዋና ነጥብ ‹ወዳጄ ልቤ›ን ቢያደርግም ስለ አሊጎሪ በቂውን ግንዛቤ ያስጨብጣል፡፡ ከኔ ጥናት ጋር፣ ስለ አሊጎሪ ምንነት እና የተጠቀሰው መጽሐፍ በሥነ ጽሑፉ ብልሃት ላይ የተጫወተውን ሚና በመጠቆም ተመሳስሎነት ቢኖረውም፣ የኔ ጥናት አብይ አላማ ግን፣ ‹‹አሊጎሪ በዘመናዊ አጫጭር ልቦለዶች ውስጥ›› የተሰጠውን ቦታና የተገለፀበት መንገድ አጉልቶ ማሣየት ነው፡፡

ጌቱ ገላዬ÷ ‹አሊጎሪና ተምሳሌት በአማርኛ ልቦለዶች ውስጥ› በሚል ርዕስ፣ በ1984 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ፣ በትምህርት ክፍሉ ከቀረቡት ጽሑፎች ውስጥ ‹‹አሊጎሪና ተምሳሌት›› ያላቸውን ሥነ ጽሑፋዊ ዋጋ በተመለከተ የቀረበ አንድም ጥናት አለመኖሩን ይገልፃል፡፡

ጌቱ የጥናቱን ዓላማ በገለፀበት ክፍል ‹‹ሁለቱ ቴክኒኮች በፈጠራ ሥራ ውስጥ እንዴት ሊከሰቱ እንደሚችሉ ለማሣየትና ሁለቱን ቴክኒኮች ለይቶ ለመረዳት የሚያስችሉ መንገዶችን ለመጠቆም መሆኑን ከመግለፁም በተጨማሪ፣ ለጥናቱ ይበጃሉ ተብለው በተመረጡ የአማርኛ ልቦለዶች ውስጥ፣ ደራስያኑ በአሊጎሪካል የአፃፃፍ ቴክኒክ ለማስተላለፍ የፈለጉትን ርዕሰ ጉዳይ›› በመመርመር በአቀራረባቸው ላይ ትንተና አድርጓል፡፡

ጌቱ÷ በጥናቱ የዳሰሳቸውና አሊጎሪያዊ ባህርያትን ይዘዋል ያላቸው የፈጠራ ሥራዎች የአፈወርቅ ገ/ኢየሱስ ‹ጦቢያ›፣ የኀሩይ ወልደስላሴ ‹ወዳጄ ልቤ› የመክብብ ደስታ ‹ያቶ መሰንበት ባልንጀርነት ታሪክና የምስጋና ግጥም› የመኮንን እንዳልካቸው ‹የቃየል ድንጋይ› እና ‹የድሆች ከተማ›፣ የጌታቸው አወቀ ‹ማኅደረ ጥበብ፣ ማስተዋል ዘመዴ›፣ የግርማ ዳመኑ ‹ድል በሰላም›፣ የመኮንን ዘውዴ ‹በመቆየት ተፀምር ዐየሁ›፣ የሀብተወልድ ወ/ስላሴ ‹ሰዎች በዓለም ገበያ›፣ የመኮንን ዘውዴ ‹ያይኔ ብርሃን›፣ ‹አስቻለው›ና ‹የዓለም ሰው እርምጃ› ናቸው፡፡ ተምሳሌትን ተጠቅመዋል ካላቸው ደራስያን ደግሞ የግርማቸው ተ/ሃዋርያትን ‹አርአያ›፣ የአቤ ጉበኛን ‹አልወለድም› የሀዲስ አለማየሁን ‹ፍቅር እስከ መቃብር›፣ የዳኛቸው ወርቁን ‹አደፍርስ›ና የበዐሉ ግርማን ‹ደራሲው› ናቸው፡፡

ይህ ጥናት ምንም እንኳን በክፍል አንድ ላይ ስለ አሊጎሪ ምንነት እና ስለጠቀሜታው የሚያነሳው ክፍል ከኔ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ቢኖረውም፣ የእኔ ጥናት ዘመናዊ አሜሪር ልቦለዶችን እንጂ ጌቴ ገላዬ የሚጠቅሳቸውን መጻሕፍት ላይ ትኩረት አያደርግም፡፡

ዮናስ አድማሱ ÷ ‹‹የንባብ የትርጓሜ ነገር ዘይቤ፣ የጦቢያ ምሳሌ›› በሚል ርዕስ የታተመው *[1] ይህ ጥናት፣ በ1900 ዓ.ም፣ በአፈወርቅ ገ/ኢየሱስ አማካይነት ለንባብ የበቃውን ‹ጦቢያ› ልብወለድን መሠረት ያደረገ ነው፡፡

አጥኚው፣ የ‹ጦቢያ› ልቦለድ አቀራረብ ተረታዊ አጀማመርና አካሄድን የተከተለ ቢሆንም፣ ደራሲው ወይም ተራኪው፣ በልቦለዱ ውስጥ ያስተላለፈውን መልዕክት፣ በምግባርና በፖለቲካ መሀል ያለውን ቁርኝት እንዴት እንዳሳየ እና ምግባርና ፖለቲካ ለማኅበረሰቡ እንዴት አስፈላጊ እንደሆኑ በክርስቲያን ወገን እና በአረመኔ ወገን በተሳሉ ገጸ ባህርያት አማካኝነት እንዴት እንደተላለፈ አሳይቷል፡፡

እንደ ዮናስ ትንታኔ፣ ከፍ ሲል የተጠቀሰውን የጭብጡ መካተቻ፣ ለተራኪውም ራዕይ መጠቆሚያ የሚሆነው፣ በልቦለዱ መዝጊያ የተጠቀሰው አገላለፅ ነው፡፡ ‹‹ባንድ ነጋዴ ሰበብ ሁሉ ዳነ፣ ባንዲት እሴት ምክንያት ሁሉ አመነ፣ ባንድ ንጉስ ቃል ኢትዮጵያ ቆመ›› የሚለውን አባባል፣ ‹‹ነጋዴ››ን የኢኮኖሚ፣ የልማት፣ ‹‹እሴት››ን የሃይማኖት፣ የምግባር፣ ‹‹ንጉሥ››ን የአስተዳደር፣ የመንግስት ምሳሌዎች (alegory) መሆናቸውን ገልጿል፡፡ እነዚህ ምሳሌዎች ደግሞ ለተደላደለ፣ ጦርነትን ለራቀ፣ ሰላምን ላፀደቀ ማኅበረሰብ አስፈላጊ መሆናቸውን ለመጠቆም እንደተጠቀሱ ያብራራል፡፡

ይህ ጥናት በጦቢያ ልቦለድ ውስጥ የተጠቀሱት ገፀ ባህርያት እንዴት እንደተሳሉ፣ ደራሲው ወይም ተራኪው በዋናነት ምግባራዊና ፖለቲካ መልዕክት ለማስተላለፍ እንዴት እንደተጠቀመባቸው ሲገልፅ፣ ድርሰቱንም በአሊጎሪያዊ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት አንፃር ይተነትነዋል፡፡

* ይህ ጽሑፍ ጦቢያ መጽሔት በመጋቢት ወር 1989 እትሙ ከማስፈሩ በፊት፣ ቀደም ብሎ በኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ በተደረገ የሥነ ጽሑፍ ጉባኤ ላይ መቅረቡ በጥናቱ መግቢያ ላይ የተገለፀ ሲሆን፣ ጽሑፉ ለመጽሔቱ በሚስማማ መንገድ ተቀንብቦ መቅረቡ አጥኚው አያይዘው ገልፀዋል፡፡

ምንም እንኳን ጥናቱ የልቦለዱን አሊጎሪያዊ ባህርይ አጉልቶ ቢያወጣም፣ እኔ ከተነሣሁበት ነጥብ አንፃር በአንድ ምክንያት ይለያል፡፡ ጥናቱ መሠረት ያደረገው ‹ጦቢያ› የተሰኘውን መካከለኛ ልቦለድ ነው፣ የኔ ጥናት ደግሞ ትኩረቱ አጫጭር ልቦለዶች ላይ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## አሊጎሪ በዘመናዊ የአማርኛ አጫጭር ልቦለዶች

በዘመናዊ የአማርኛ አጫጭር ልቦለዶች ውስጥ የአሊጎሪ ምንነት የሚታይባቸው አጫጭር ልቦለዶች (Short Stories) በርካታ ባይሆኑም፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን አሊጎሪን እንደ አንድ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት የሚጠቀሙ የአንጋፋ፣ የጎልማሳና የወጣት ደራስያንን ሥራዎች እያነበብን ነው፡፡

በዚህ ጥናቴ ዋነኛ ምእራፍ ውስጥ በእነዚህ ስድስት ደራስያን ማለትም በስብሃት ገ/እግዚአብሔር፣ በአዳም ረታ፣ በአማምነው ባረጋ፣ በአለማየሁ ገበየሁ እና በሚካኤል ሺፈራው የተደረሱ ልቦለዶችን እዳስሳለሁ፡፡

‹የአሊጎሪ ምንነትና የአሊጎሪ ጠቀሜታ› በሚለው በምእራፍ ሁለት ንኡስ ርዕስ የሰፈሩትን ሃሣቦች መነሻ በማድረግ፣ ከላይ የተጠቀሱት ደራስያን ሥራዎች አሊጎሪን እንዴት እንደተጠቀሙበት፣ ገፀባህርያቱን እንዴት እንደ ቀረፁዋቸውና በከፊል በገፀባህርያቱ አማካይነት ማስተላለፍ የፈለጓቸውን ሞራላዊ፣ ሥነ ምግባራዊ፣ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ መልዕክቶችን እና አመለካከቶችን ይዳስሳል፡፡

### 3.1. አሊጎሪ በስብሃት ገ/እግዚአብሔር አጫጭር ልቦለዶች

ለዚህ ጥናት የተመረጡት፣ የደራሲው ሥራዎች፣ ሁለት ሲሆኑ እነሱም ‹ቢራቢሮ› እና ‹አውራ ዶሮው› ናቸው፡፡

እነዚህ አጫጭር ልቦለዶች ‹አምስት ስድስት ሰባት› ከተሰኘው ከደራሲው መድበል የተወሰዱ ሲሆን፣ መድሐፉ ለመጀመሪያ ጊዜ ለህትመት ሲበቃ (1981)፣ 10 ልቦለዶች ተካተውበት የነበረ ቢሆንም፣ በድጋሚ ሲታተም (2000 ዓ.ም) ተጨማሪ 15 ልቦለዶች ይዞ ወጥቷል፡፡ ‹ቢራቢሮ› እና ‹አውራ ዶሮው› ከተካተቱት መሃል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

### 3.2.1. ቢራቢሮ

ቢራቢሮ የሚለው አጭር ልቦለድ ÷ አምስት ስድስት ሰባት በሚለው መድበል ላይ ከገፅ 200-205 ባሉት ገጾች መሀል የሚገኝ ነው፡፡ ትረካው የተፃፈበት ዘመን አልተገለፀም፡፡ መጀመሪያ አፅመ ታሪኩን ቀጥሎ ደግሞ ትንታኔው እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

#### 3.2.1.1. አፅመ ታሪክ

‹ቢራቢሮ› በሚል ርዕስ የቀረበው ይህ አጭር ልቦለድ ጠላቶቿን የምትከላከልበት ምንም አቅም ስለሌላት ስለ አንዲት ቢራቢሮ እና ወዳጅና ጠላቶቿ የሚተርክ ነው፡፡ ቢራቢሮዋ አደጋ ቢገጥማት የምትሸሽግበትና የምትከላከልበት አቅም ስለሌላት፣ ከዕለታት አንድ ቀን እግዜርን ለመማፀን ወደ መንበሩ ትቀርባለች፡፡ እንደሌሎች ፍጥረታት ፣ ጠላቶቿን የምትገዳደርበት እንደ ጥርስ፣ ቀንድ፣ ወይም መርዝ ያለ ራስን መከላከያ ስለሌላት የሞት መላዕክት በየትኛውም ጊዜ ነፍስዋን ሊነጥቅ እንደሚችል ስለሚሰማት ይህንን ልትነግረው ነው ጉዞ የጀመረችው፡፡

ቢራቢሮዋ ወደ ፈጣሪ ዘንድ ቀርባ ጉዳይዋን በማስረዳቷ ፈጣሪ የጠየቀችው ይሟላላት ዘንድ፣ ከአንድ ትልቅ ቅርጫት ውስጥ፣ ይጠቅመኛል ብላ የምታምንበትንና የምትፈልገውን ሁሉ እንድትወስድ ይጋብዛታል፡፡ ቅርጫቱ ውስጥ ከሚገኙት ነገሮች ጠላትዋን ማጥቃትና፣ ሞትን ማስበርገግ ይችላሉ ብላ ካመነችባቸው መሣሪያዎች መሐል የሾሉ ጥርሶች፣ ሹል ጦር እና ጨኸት አገኘች፡፡

እነዚህን ይዛ ወደ ምድር ወረደች፡፡ በጉዞዋም ቢራቢሮዋ በደማቅ ቀለሟና በተዐምራዊ መዐዛዋ የማረከቻት አንዲት አበባ አግኝታ ልትበላት ጓጓች፡፡ ተጠጋቻትም፡፡ ከእግዜር ዘንድ ያመጣችው የሾሉ ጥርሶች ግን ውሃዋን አላስጠጣ አሉዋት፣ አበባዋም ተቦጫጨቀች፡፡ በዚህ ጊዜ ቢራቢሮ፣ የፈለገችውን እንዳታገኝ እንቅፋት ሆኖባታልና የጥርሱ አስፈላጊነት አልታይሽ አላት፡፡ በህይወት ዘመኗ ለአንድም ቀን ቢሆን በጥርስ የሚታኘክ ምግብ እንደማትጠቀም አሰበች፡፡ ለማቅ

ፈገግታም ቢሆን፣ ሣቅና ፈገግታዋ ከንፏና በረራዋ ውስጥ እንዳለ አምና፣ ጥርሱን እንደ ትርፍ ሸክም ቆጥራ ትተወዋለች፡፡

ቀጥሎ ደግሞ ቢራቢሮዋ አንድ ድምቢጥ አጋጠማት፣ ድምቢጡ ጠላት ነውና፣ እሱ ሣይገድላት በፊት ልቅደመው ብላ በፍጥነት ጦሩዋን ሰበቀችበት፡፡ ድምቢጡ ሞተ፡፡ ጦሩን ከአስከሬኑ ለመንቀል ስትፍጨረጨር ጦሩ ከተሰካበት አልነቃነቅና አልነቀል አላት፣ የድምቢጡ የደም ክርፋትም እረፍት ስለነሣት ጦሩን እዚያው ትታው ለመሄድ ወሰነች፡፡

እስከአሁን ከፈጣሪ ተቀብላ፣ ራስዋን ለመከላከል ይጠቅመኛል ብላ ካመጣቻቸው ሥጦታዎች ያልሞከረችው ጩኸትን ነበር፡፡ ይህንንም የጩኸት ድምጽ ለመጠቀም እስኪመሽ ቆየችና፣ ፍጥረታት ዕረፍት በሚወስዱበት ሰዐት ከአንበሳ ሰባት ጊዜ የሚልቅ ጩኸትዋን ለቀቀችው፡፡ ፍጡራንም በረገጉ፣ አካባቢዋም መረበሽ በዛበት፡፡

ቀስ በቀስ ግን በጩኸቱ የተነሣ ተረብሸውና ተበታትነው የነበሩ ነፍሣት ወደየሥፍራቸው ተመለሱ፡፡ ስለተሰማው ጩኸትና ስለተፈጠረው ድምፅ ሲወያዩ እሷ ብቻ እንዳልበረገገች ስትናገር ግን የሚያምናት አጣች፡፡ ለበምስክርነትም ሸረሪት ትጠየቅ አለች፣ ሸረሪትም መሰከረች፡፡ እንደሚታወቀው ሸረሪት አደጋ ሲያጋጥማት ራስዋ በሰራችው ድር ትሸሸጋለች እንጂ ሥፍራዋን አትለቅም፡፡ እናም በአደጋው ጊዜ የጮኸችው እሷ ራሷ መሆኗን ስትናገር ሸረሪቷ አላመነቻትም፡፡ በመጨረሻም ያ አስበርጋጊ ጩኸት ከቢራቢሮዋ ክንፍ አካባቢ ተፈትልኮ መውጣቱን ስታውቅ ሸረሪት እኔም ጩኸቱን 'ካልሞርኩት' ትላለች፡፡

ቢራቢሮዋ ከሸረሪት ጋር ተስማምታ ጩኸቱን ታስሞክራታለች፡፡ ለውለታዋም ምላሽ እንዲሆን ሸረሪትዋ የራስዋን የሸረሪት ድር ጥበብ እንድትጠቀምበት ትሰጣታለች፡፡ ሸረሪት ግን በድሯ ላይ ትንሽ እንደተወዛወዘች ይሰለቻትና ድርዋን ትመልስላታለች፡፡ ቢራቢሮም ቀደም ሲል ጩኸቱን እኔ ራሴ ጮኼው አልጠገብኩትም ብላ የነበረ ቢሆንም፣ ቀስ በቀስ ግን ጩኸቱ ይሰለቻትና ጩኸቱን ትርፍ ሸክም ነው ብላ ትሰጣታለች፡፡ ሸረሪቷም ጩኸቱን እያከራየች መኖር ስትቀጥል ታሪኩ ይጠናቀቃል፡፡

### 3.2.1.2. ትንታኔ

*ቢራቢሮ* በቢራቢሮ ልቦለድ ውስጥ ባህርይዋን ባትለቅም አንዳንድ የምታደርጋቸው ድርጊቶች ግን ሰውን የሚወክሉ ናቸው፡፡ እንደ ሰው ፍርሃት ይጐበኛታል፤ እንደ ሰው ተስፋ መቁረጥ ይንጣታል፤ እንደ ሰው መሰልቸት ይሰማታል፤ ትፀልያለች፤ ትሰለቻለች፡፡ (ገፅ 200)፡፡ በዚህም ገፀ ባህርይዋ ሰውኛ ተደርጋ መቅረቧን ብቻ ሳይሆን ታሪኩ የተምሳሌት ዘይቤ መከተሉን እንረዳለን፡፡

ብዙውን ጊዜ ቢራቢሮ በአንድ ትረካ ውስጥ የምትወክለው ‹መልዕክተኛ›ን ነው፡፡ ቢራቢሮ እንደ መላዕክት ሰውን ከፈጣሪ ጋር የማገናኘት አቅም እንዳላት ልዑክ ውክልናዋን ይሰጧታል፡፡ በዚህ አጭር ትረካ ውስጥም ቢራቢሮ ከሌሎች ፍጥረታት በተሻለ መንገድ (ታሪኩ ውስጥ ከሚጠቀሱት ከነድንቢጥ፤ ኤሊ፤ ሱፍ አበባ እና ሽረሪት ይልቅ) ወደ ፈጣሪዋ ደጅ ቀርባ ጉዳይዋን የማስደመጥ ድፍረት አላት፡፡ ወደ ፈጣሪ ሄዳ ቅሬታዋን ለማሰማት ዝግጁ እንደሆነች ለሱፍ አበባ ስትነግራት፤ ሱፍ አበባም ያላንዳች ማመንታት ነው፤ በህይወት ዘመኗ እንዲመለስላት የምትፈልገውን ጥያቄ የምታስከትለው፡፡ «... ቀን ቀን ባለሁበት ቆሜ ፀሃይን ስከተል እውላለሁ፡፡ ሌሊት ሌሊት ባለሁበት ተደፍቼ ጸሀይን ስናፍቅ አድራለሁ፡፡ እባክህን እዘንልኝ፤ ራራልኝ በይልኝ›› (ገፅ 201)

ቢራቢሮዋ ያስፈልጉኛል ብላ የምታምንባቸውን የጦር መሣሪያዎች በህይወት ስትኖር ሲያስፈልጓት አናይም፡፡ ስጦታዎቿን ይዛ ወዳገሯ ስትመለስ ይርባታል፡፡ በዚህ ጊዜ አንዲት ውብ አበባ ታገኛለች፡፡ አበባዋን ለመመገብ ግን ጥርሶቿ ይከለክሏታል፡፡ በደማቅ ቀለሟና በተዐምራዊ መዐዛ የምትጣራውን አበባ ለመመገብ ብትፈልግም፤ ከአበባዋ የምትፈልገውን አላገኘችም፤ ይልቁንስ አበባዋን በጫጨቀቻት፡፡ የምትመካባቸውን ጥርሶቿንም ወዲያ አሽቀንጥራ ጣለቻቸው (ገፅ 202)፡፡ በተደጋጋሚ ጊዜ ጥቃት ያደርስባትና ለህይወቷ ስጋት የሆነባት ድንቢጥንም በተሰጣት ሹል ጦር ደረቱ ላይ ሠንቅራ ከዚህ ዓለም በሞት ብትገላግለውም፤ የሰካችበትን ጦር ለመንቀል አቅም አንሷት፤ የደሙ ክርፋት ረብሿት፤ ጦሩን እዚያው ትታ ትሄዳለች (ገፅ 202)፡፡ በውድቅት ሌሊት፤ ፍጡራን እረፍት በሚያደርጉበት በእንቅልፍ ዓለም በሚመላለሱበት ጊዜ፤ ከፈጣሪ ዘንድ

የተረከበችውን ጨኸት በምትጮሀበት ጊዜ፣ ለጊዜው ፍጥረታትን ብታስደነግጥም፣ በሽረሪት ዘንድ መከበርን ብታተርፍም፣ በመጨረሻው ሰዐት ግን ጨኸትዋን ታውሳታለች፡፡ እሷ ራሷ ሳትጠግበው፡፡ ‹‹ተይ! ተይ! እንዴ ብቻ? እሺ እንለዋወጥ፡፡ ያንቺን ጨኸት ላንዴ ብቻ ስጪኝ፣ የኔን ድር ጥበብ እሰጥሻለሁ፡፡ አቤት አንዴ ብትወዛወዢ! በኔ ድር! ሸረሪት በሆንኩ ትይ ነበር፡፡›› ትላታለች ሸረሪት (ገፅ 205)፡፡ ቢራቢሮ የጓደኛዋን ፍቃድ ለመፈፀም ዝግጁ ብትሆንም፣ ጥቂት በድሩ ተወዛውዛ ይሰለቻታል፡፡ ጨኸቱንም ሸረሪቱ እንድትጠቀምበት አሳልፋ ትሰጣታለች፣ ‹ደግሞ ጨኸት ምን ያደርግልኛል› ብላ (ገፅ 205) ፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ቢራቢሮ ከፈጣሪ የተረከበቻቸውን ስጦታዎች በጥንቃቄ ስትይዛቸው እና በአግባቡ ስትጠቀምባቸው አናይም፡፡ ለምና እና መርጣ ያገኘቻቸውን ሶስቱን የጦር መሣሪያዎች አስፈላጊነታቸው አልታይሽ ይላታል፡፡

በዚህ ትረካ ውስጥ በመሪ ገፀ ባህርይነት የምናገኛት ቢራቢሮ፣ ከላይ ከተገለፀው መልዕክት አድራሽነት ውጪ በነፍስ ልንመስላት እና ነፍስን ወክላ የምትቆም መሆኗን የሥነ ጽሑፍ ተንታኞች ይገልፃሉ፡፡

በዚህም መሰረት፣ ቢራቢሮዋ ለውክልና የቆመችው እንደ መላዕክት፣ መልዕክት የማድረስን ሚና ልትጫወት ነው ብለን ስናምንም ከላይ የተጠቀሱትን ምሳሌዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡[2]

ደራሲው፣ ይህን ‹ቢራቢሮ› የተሰኘችዋን ትረካ በአሊጎሪ አቀራረብ በመጻፍ፣ ነፍሳችን የሚያስፈልጋት ነገር እስከዛሬ የነበሩዋት ቀደም ሲል የተሰጡዋት ነገሮች እንደሆኑ፣ ስንፈጠር የተሰጡን የተፈጥሮ ፀጋዎች ስለሚያስፈልጉን እንጂ ለሌላ እንዳልሆነ፣ እንዲኖሩን የምንመኛቸው ተጨማሪ ነገሮች ሁሉ፣ ፀሎታችን ተሰምቶ ቢሰጡን እንኳን ብዙ ሣንጠቀምባቸው እንደሚሰለቹን ለማሳየት የተፃፈ አጭር ልቦለድ ነው፡፡

### 3.2.2. አውራ ዶሮው

[2] ‹Some times a butterfly is a messenger, a kind of angel, that brings grace of a change of heart› (suttee, 2006)

ይህ ትረካ *አምስት ስድስት ሰባት* ከሚለው የደራሲው የአጫጭር ልቦለዶች መድበል የተወሰደ ሲሆን የሚገኘውም ከገፅ 219-225 ነው፡፡ መጀመሪያ አፅመ ታሪኩን ቀጥሎ ደግሞ ትንታኔው እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

### 3.2.2.1. አፅመ ታሪክ

‹አውራ ዶሮው› ስለ አንዲት ድመት እና ቤተሰቧ ስለሆነው አውራ ዶሮ እንዲሁም ስለ አሳዳጊዎቻቸው የሚተርክ አጭር ታሪክ ነው፡፡ ጌታ በህማማት ሰሞን፣ በዕለተ ሐሙስ፣ ራሱን ለጠላት እጅ አሳልፎ ከመስጠቱ በፊት ሙሴ ተብሎ ከሚጠራው አውራ ዶሮ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ነው፡፡ አውራ ዶሮው የእትዬ አልታዬ ነው-ንብረትነቱ፡፡ እትዬ አልታዬ 'ሙሴ' የሚል ስም ካወጡለት አውራ ዶሮ ሌላ፣ 'ፈርኦን' ብለው የሚጠሩት ድመት እና ሌላ 'እማሆይ' የምትባል ዶሮ አሏቸው፣ እትዬ አልታዬ ፈርኦን እና እማሆይን እንደ ልጆቻቸው ነው የሚያዩዋቸው፣ የሚያማክሯቸው፣ የሚያጫውቷቸው፡፡ መሐን ናቸው- እትዬ አልታዬ፡፡

እትዬ አልታዬ ከልባቸው የሚመላለሰውንና፣ በሃሳባቸው የሚንሸራሸረውን ሁሉ ለፈርኦን ይነግሩታል፡፡ ፈርኦን ‹ሚያው› ከሚል ድምፅ ውጭ ሌላ አይወጣውም፡፡ ምንም እንኳን ‹ሚያው› ከሚለው ድምፅ ውጪ ሌላ ቃል ሲናገር ባይደመጥም እትዬ አልታዬ እያንዳንዱን የድመቱን ሚያው ማለት ይተረጉሙታል፡፡ ፈርኦንን ይመክሩታል፡፡ ዓይጧን አድኖ የጭንቅ ሰዐቷን ከሚያራዝም ይልቅ ባንድ ጊዜ ገድሎ ቢበላት እንደሚሻል፣ ከዚህ የተሻለው ሃሳብ ደግሞ ዓይጥ ማደኑን ትቶ እሣቸው የሚያዘጋጁለትን የበሰለ እሣት ያየው እህል መመገብ እንዳለበት ያሳስቡታል፡፡

የእትዬ አልታዬ ሌላኛው ልጅ 'ሙሴ' ደግሞ ኢየሱስ ሊሰቀል አንድ ቀን ሲቀረው አግኝቶታል፡፡ በዚያች ሌሊት አውራ ዶሮው ስንት ሰዐት መሆኑን ለማብሰር ዝግጁ ሆኖ ካብ ላይ ሲወጣ ድንገት ብርድ ብርድ ይለዋል፡፡ ብርዱ ከየት ሊመነጭ እንደቻለ ግራ ቀኙን ሲያማትር 'ሰውየው' የፍርሃት ብርድ ተከናንቦ እና ተጀቡኖ ፈንጠር ብሎ ተቀምጧል፡፡

አውራ ዶሮው የሰውየውን ፍርሃት አይቶ ከሞት ሊያስመልጠው ማምለጫ መንገዶችን ቢያመላክተውም፣‹ሰውየው› ግን መሞት ስላለብኝ ማምለጥን አልሞክረውም ይለዋል፡፡ አውራ ዶሮው የ‹ሰውየው› ሞትን እየፈሩ መጥቶ እስኪወስዳቸው ድረስ መጠበቅ አልተዋጠለትም፡፡ ሰውየው ግን ሌሎች ፍጡራን ይድኑ ዘንድ ራሱን ለሞት አሳልፎ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን ይነግረውና እንዲተኛ ያሰናብተዋል፡፡

አውራ ዶሮው ግን ከ‹ሰውየው› ከተለየ በኋላ እንቅልፍ አይወስደውም፡፡ የሰውየውን ፍርሃት እያሰበ እንቅልፍ ካይኑ ራቀበት፡፡ እናም ወደነበረበት ተመልሶ ሌሎች ይድኑ ዘንድ ራሱን ለሞት አሳልፎ ለመስጠት ዝግጁ የሆነውን ሰው ያገኘዋል፡፡ አሁንም ነገ እንደሚገድሉት አውቆ በፍርሃት ተጀቡኖ የጉሀ መቅደድን እየጠበቀ ነው፡፡ አውራ ዶሮው አሁንም ከገዳዮቹ እንዲያመልጥ ይመክረዋል፤ የራሳቸውን ሞት ራሳቸው እንዲሞቱ ለምን አትተውላቸውም ይለዋል፡፡ ‹ሰውየው› ግን መሞቱ ግድ ስለሆነና የመሞቻ ቀኑም ዛሬ ስለሆነ፤ ሃሣቡን ይቃወመዋል፡፡ አውራ ዶሮው በ‹ሰውየው› ሁኔታ ደስተኛ አልሆነም፤ መሞት የፈለገበት ምክንያት አላሳመነውም፤ እናም አሁንም ሊረዳው ይፈልጋል፤ ማምለጫ መንገድ ሊጠቁመው፡፡ ካሁን አሁን ሃሳቡን ይቀይር ይሆናል በሚል ስሜትም፤ የመጮኺያ ሰዐቱን ከተለመደው በአስራ አምስት ደቂቃ ያራዝመዋል፡፡

አውራ ዶሮው ‹ሰውየው›ን ለማዳን የሚያደርገው ትግል ሳይሣካለት ቢቀርም በሰውየው ልቦና ውስጥ ግን አውራ ዶሮው ሞት 'ባይቀርም ቢዘገይ ይሻላል' በሚል ስሜት መሞላቱን ሲያውቅ፣ ፊርቹ ስለደረስክልኝ ሞት አይድረስብህ ብሎ ይመርቀዋል፡፡ አዲስ በረከትም ያድለዋል - ሞትን ድል ነስቼው ስመለስ መምጣቴን የምታበስር አንተ ነህ ብሎ፡፡

በሦስተኛው ቀን ሰውየው ሞትን ድል አድርጎ መቃብር ፈንቅሎ ሲነሣ በአውራ ዶሮው ጩኸት ነበር ትንሣኤው የተበሰረው፡፡

የ‹ሰውየው› ትንሣኤ ከተበሰረ በኋላ ሐዋርያት በተሰበሰቡበት ተገኝቶ፤ ጥንድ ጥንድ ሆነው ወንጌልን እንዲሰብኩ ሃላፊነት ከሰጣቸው በኋላ ለአልዓዛር እና ለማርያም መግደላዊት አንድ ሃላፊነት ጣለባቸው፤ የጭንቅ ሰዓት አጋሩን አውራ ዶሮውን

እንዲጠብቁ፡፡ ዶሮው መግደላይት ቤተክርስቲያን ሲኖር ቆየና አንድ ቀን ማንም ሳያዝዘው፣ ከእንግዲህ በኋላ ያንቺ ነኝ ብሎ ከእትዬ አልታዬ ጋር መኖር ጀመረ፡፡

3.2.2.2. ትንታኔ

ትረካው፥ ምንም እንኳን እትዬ አልታዬ የተባሉ መሐን ስለሚያሳድጉዋቸውና እንደ ልጆቻቸው ስለሚቆጥሯቸው የቤት እንስሳት ቢተርክም (አሊጐሪ ነውና ላይ ላዩን ሲያዩት ይህን ይመስላል)፣ በዋናነት የሚያተኩረው ግን የብሉይ እና ሀዲስ ኪዳንን ታሪክ እንድንፈትሽ የሚያደርግ ነው፡፡

ትረካው ሦስት ክፍሎች ሲኖሩት፣ የመጀመሪያው 'አሀዱ' በሚል ርዕስ የቀረበው እትዬ አልታዬ ከድመታቸው ጋር የሚያደርጉት እናታዊ ተግሳፅ፣ ሁለተኛው 'ክልኤቱ' በሚል ርዕስ የቀረበው ደግሞ 'አውራ ዶሮውና ሰውየው' በሚል ርዕስ፣ ክርስቲያኖች እንደሚያምኑት ኢየሱስ በፀሎተ ሐሙስ ራሱን ለዓለም መድኃኒትነት አሣልፎ ከመስጠቱ በፊት ይታይበት ስለነበረው ፍርሃትና ሞትን ለመቀበል ስለነበረው ዝግጁ መንፈስ ሲተርክ[3]፣ ሦስተኛው ክፍል ደግሞ አውራ ዶሮው ከክርስቶስ ትንሣዔ በኋላ ስለነበረው ዕጣ ፈንታ ያወጋናል፡፡

በመጀመሪያው ክፍል ላይ ያለውን ድመት፣ እትዬ አልታዬ ፈርኦን ብለው ነው የሚጠሩት ፡፡ ፈርኦን፥ በብሉይ ዘመን የነበረ የግብጻውያን ንጉስ መጠሪያ ነው፡፡ በፈርኦናውያን ዘመን የሕዝባዊ አገዛዝ ሥርዓቱ ያልሰለጠነ ነበር - ዓይን ላወጣ ዓይን፣ ጥርስ ላረገፈ ጥርሱ እንዲረግፍ የሚደረግበት ዘመን ነበር፡፡

እትዬ አልታዬ ለድመታቸው ፈርኦን የሚል ስያሜ መስጠታቸውም የውክልና ፍቺው የብሉይ ዘመንን ሕይወት እንድናስታውስበት ይመስላል፡፡ የድመቱ ባሕርይ የሚወክለው ይህንን ነው፣ እትዬ አልታዬ ከድመቱ ባሕርይ ያልወደዱት በዓይጥ ላይ የሚወስደውን ቅጥ ያጣ ርምጃ ነው፡፡ ድመቱ ዓይጡን አጥምዶ ወይም አድብቶ ከያዘ በኋላ፣ አንክቶ እንደመብላት፣ የሥቃይ ጊዜውን በማራዘም፣ የደስታ መጠኑን ከፍ እንደሚያደርግ ከእትዬ አልታዬ ተግሣፅ ለመረዳት እንችላለን፡፡

---

[3] ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 19ን ልብ ይሏል።

እንደሚታወቀው ድመቱ - ስሙም ፈርኦን ተብሏልና - በጭካኔ ላይ የተመሰረተ አገዛዝ ነው የሚከተለው፡፡ ደራሲው ፈርኦን የሚለውን ስም ለሌላ አጭር ልቦለድ ገፀ ባህርይነት ሲጠቀም እንዳነበብነው[4] ፈርኦን መኳንንታዊ ባህርይ ቢኖረውም፣ አመራሩ በጭካኔ የተሞላ ነው፡፡ የአገዛዝ ዘመኑ በመቁረጥ፣ በመፍለጥና ደም በማፍሰስ የተሞላ ነው፡፡ ዓይጥ የተፈጠረው በድመት ለመበላት እንደሆነ የሚያምን ነው፣ ሕዝብም የተፈጠረው በፈርኦኖች ለመገዛት፡፡

እትዬ አልታዬ በዚህ አይከራከሩትም፡፡ የእሣቸው ጭንቅ ዓይጥ መሞቱ ላይቀር ለምን የፈርኦን መጫወቻ ይሁን ነው፡፡ ወዲያው ሞቱን ሰጥቶ መገላገል ሲቻል፣ እየነከሱ፣ እያሰቃዩ ማቆየቱን አልወደዱትም፡፡ በርግጥ ምክራቸውን የተቀበለ ይመስላል፡፡ ከድመቱ አፍ የሚወጣው ቃል 'ሚያው' ብቻ ቢሆንም፣ የድመቱን ድምፅ ሰምተው፣ ድምፁን ወደ ቃላት ይተረጉሙታል፡፡ እናም ምክራቸው ተቀባይነት እንዳገኘ አምነው 'ጐሽ' ቢሉትም ድመቱ ላይ ግን አንድ ጥርጣሬ አላቸው፡፡ '. . . ሁሌም እሺ ነው መቸስ፡፡ እምቢ አይወጣህም፡፡ እሺ እያልክ ብቻ የልብህን ማድረስ፡፡' (ገጽ 220)፡፡

በርግጥ ፈርኦን ከሙሴ ጋር አይጋጭም፡፡ ሙሴ የእትዬ አልታዬ ሌላኛው ቤተሰብ ነው፣ አውራ ዶሮ፡፡ የአውሮ ዶሮው እትዬ አልታዬ ግቢ ውስጥ መገኘት ድንገቴ ነው፡፡ ከልጅነቱ ጀምሮ ከነፈርኦን ጋር ያደገ አይደለም፡፡ '. . . የሚያስደንቅ ህብረ ቀለማት ላባ ተላብሶ የተከሰተ፡፡' (ገጽ 220)፡፡ የብሉይ ኪዳኑ ሙሴ አመጣጡ እንደ ክስተት ነው፣ አስርቱን ትዕዛዛት ከሲና ተራራ ይዞ ሲመጣ፣ ሕዝቡ የተደላደለ እና ከፈርኦናዊ አገዛዝ ነፃ የወጣ እንዲሆን ሲያደርግ፣ እያንዳንዱ ባጠፋው ጥፋት ልክ ትክክለኛ እና አቻ የሆነ ቅጣት እንዲሰጠው መመሪያ ሲደነግግ ለነበረበት ዘመን እንደ ድንገተኛ ክስተት ነበር[5]፡፡ ተከታይ የበዛለትም፣ ለአምልኮ በቀረበ ፍቅር ሕዝብ የተንበረከከለትም ለዚሁ ነው፡፡

በትረካው ውስጥ ያለው አውራ ዶሮም የሚወክለው ሙሴን ነው፡፡ እንደ ትዕምርት ሆኖ የቀረበው ሙሴ ብሉይ ኪዳንን ነው የሚያስታውሰን፡፡ አውራ ዶሮው ከሰውየው

---

[4] ለምሳሌ ‹ፈርኦን ሲሶ ዝና› የተሰኘውን አጭር ልቦለድ መጥቀስ ይቻላል፡፡ (አምስት ስድስት ሰባት፣ 1998)

[5] ኦሪት ዘፀጥረት ምዕ. 20

ባህርይና ዕውቀት ስሙም ሊሆን ያልቻለው፣ ሁለቱም በዘመናቱ የተላኩ የዕድቅ ባለሙዋሎች፣ የፈጣሪ መልዕክተኛ ቁሣሮች ቢሆንም፣ ለሕዝብ ያላቸውን ፍቅር ለመግለፅ የሚመላለሱባቸው መንገዶች አይመሳሰሉም:: ለዚህም ነው - ሙሴ - አውራ ዶሮው ሙሴ - ሁሉም የራሱን ሞት እሱ ራሱ እንዲሞት እንጂ ሌላ ሰው ሊሰቀልለት፣ ሊገደልለት እንደማይገባ የሚያምነው::

"ኩኩሉ! አንተ ሰው፣ ኧረ ባክህ አሁንም ለማምለጥ ትችላለህ፣ ና ሂድ ኧረ ባክህ!"
"መሞቱን መርጩው ነው፣ አይዞህ አትፍራልኝ"
"አንተ ስትፈራ እየሰማሁህ!"
"ካልፈራሁትማ ምኑን ሞትኩላቸው"
"ግን ለምን አትተውላቸውም? ራሳቸው ሞታቸውን ይሙቱት"
"እሱማ አይቀርላቸውም"
"እንግዲያማ?"
"ሂድ ተኛ፣ ተባረክ!"
"እዚህ እንደዚህ ትቼህ ሂጄ እንዴት እተኛለሁ?"
"እኔ ሞቼ ለነሱ የዘላለም ህይወት ልገዛላቸው ነው"
"ይህ እንዴት ይሆናል?"
"ሲሆን ታየዋለህ:: በል ሂድ ተኛ" /ገፅ 222-223/

በአውራ ዶሮው በሙሴና በሰውየው መሃከል ያለው ልዩነት ይኼ ነው:: አውራ ዶሮው ሰውየው ንፁህ እንደሆነ አምኗል:: ነውር ያልፈፀመ በደል ያልተገኘበት መሆኑን ከልቡ ተቀብሏል:: ገዳዮቹ ግን ሊሠቅሉት ዝግጁ ሆነዋል:: ሰውየውም የመሞቻ ሰዐቱን በፍርሃት ተውጦም ቢሆን እየተጠባበቀ ነው:: 'ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፣ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ[6]› ሆኗል::

ይህ አሊጎሪያዊ ትረካ መልዕክቱ ለቆሙለት ዓላማ ሣያፈገፍጉ ስለመወጣት ነው:: ተልዕኮን ፈፅሞ፣ ሃላፊነትን ተወጥቶ ስለመኖር፣ የፍርሃት ወጀብ ሳያሸንፋቸው እስከመጨረሻው ድረስ በመጋደል ዓላማን በፅናት ስለመወጣትና ታሪኩ የሚያትተው::

ድመቱ፥ በእትዬ አልታዬ ተመክሮ ፈርኦናዊ ባህርዩን አልተወም፣ ምክር ሰሚ ይምሰል እንጂ የአበው ልማዱን ትቶ አይጥን ከማደን፥ አድኖም ከመብላት

[6] ኢሣ 53

የማይመለስ መሆኑን አሣይቷል፡፡ አውራ ዶሮው ሁኔታዎችን ላመቻችልህና አምልጥ ቢለውም ሰውየው ግን አውራ ዶሮውን አይሰማውም፡፡

በትረካው ውስጥ አውራ ዶሮው አሊጎሪ ገፀ ባህርይ እንደሆነ የሚያሣይ ምልክቶች አሉት፤ አንደኛ ድመቱም ሆነ አውራ ዶሮ የወከሉት ሀዲስ ኪዳን ከመምጣቱ በፊት የነበረው የብሉይ ዘመንን ሕይወት ያሣያል - ከላይ እንደተጠቀሰው፡፡ ደራሲው እነዚህን እንስሳት ሲያናግር /በተለይ አውራ ዶሮ/ በሰው ባህርይ ውስጥ የሚታዩ ዓይነት ስሜቶች እንደ መገረም፡ መፍራት፡ ግራ መጋባት ያሉ ስሜቶች እንዲታዩበት አድርጓል፡፡ እነዚህ ስሜቶች በቀጥታ ማለትም ቃል በቃል ሠፍረው የተገኙ ባይሆንም፤ ከገፀ ባህርያቱ ምልልስ የምንረዳው አውራ ዶሮው የሰው ልጅ ረቂቅ ስሜቶች የሚያንፀባርቅባቸውን የሀዘን፡ የደስታና የሌሎችም ስሜቶች መገለጫዎች ይታዩበታል /. . . መሞቱን መርጨው ነው፡ አይዞህ አትፍራልኝ (ገፅ 222) ይለዋል - ሰውየውም፡፡

በአጠቃላይ ትረካው በሰውኛ የተፃፈ እና የተምሳሌት ዘይቤን ያካተተ፤ ድመት ብሉይ ኪዳንን አውራ ዶሮ ደግሞ አዲስ ኪዳንን ወክለው እንዲናገሩ ያደረገ ታሪክ ነው፡፡

## 3.3. አሊጐሪ በአዳም ረታ አጫጭር ልቦለዶች

‹የአበቦች ታሪክ›÷ ‹ማህሌት› (ሥዕል በብጥስጣሽ ጨርቆች ላይ) በሚለው የአዳም ረታ አጫጭር ልቦለዶች ላይ የተካተተ አጭር ትረካ ነው፡፡

መጽሐፉ የታተመው በ1981 ዓ.ም ሲሆን፤ በ2002 ዓ.ም በድጋሚ ሲታተም ደራሲው ከዚህ ቀደም ከሌሎች ደራስያን ጋር በመሆን ከአሣተመው ‹አባ ደፋር› መድበል ላይ አካትቷቸው የነበሩትን አራት ልቦለዶችን እና አንድ አዲስ አጭር ልቦለድ እንዲካተቱ አድርጓል፡፡

መጽሐፉ በአጠቃላይ 16 አጫጭር ልቦለዶችን ይዟል፤

### 3.3.1. *የአበቦች ታሪክ*

ለዚህ ጥናት የተመረጠው *የአበቦች ታሪክ* የተሰኘው ትረካ ከገፅ 117-128 ባሉት ገጾች የተስተናገደ ነው፡፡ መጀመሪያ አፅመ ታሪኩን ቀጥሎ ደግሞ ትንታኔው እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

#### 3.3.1.1. አፅመ ታሪክ

*የአበቦች ታሪኩ* ዐፈር በተሞላ የፕላስቲክ መደብ ላይ ኑሮዋን አመቻችታ ስትኖር የነበረች አንዲት አበባ፣ ንፋስ ህልውናዋን ሲፈታተናት የሚያሳይ አጭር ትረካ ነው፡፡ አበባዋን የተከለቻት ልጃገረድ ጠዋት ተነስታ ውሃ የምታጠጣትና የሚያስፈልጋትን እንክብካቤ ስታደርግላት የቆየች ቢሆንም ታሪክ በሚተረክበት ቀን ግን በልጃገረዷ አልተጎበኘችም፡፡

የለመደችውን ትኩረት የተነፈገችው አበባ፤ የልጃገረዷን መምጣት በናፍቆት ትጠባበቃለች፡፡ በልጃገረዷ አማካይነት ውበቷን ወደ አደባባይ ይዛ ለመውጣት እጅጉን ተመኝታለች፡፡

የውርጩ እየበረታ መምጣት ልጃገረዷን ከቤትዋ እንዳትወጣ እንቅፋት እንደሆነባት ጠርጥራለች፡፡ እሷንም ይበርዳት ጀምሯል፡፡ በዚህ መሀል ነው፤ መምጣቱን ልብ ያላለችው ንፋስ ከተተከለችበት ዐፈር ላይ በጣጥሶ ሊጥላት ቆርጦ መነሳቱን የሚነግራት፡፡

በአበባዋ ላይ እንዲህ አይነቱን ርምጃ ለመውሰድ ንፋስ ቆርጦ የተነሳው ‹መንገዴ ላይ ተደቅነሻል፣ እንቅፋት ሆነሽብኛል› ብሎ ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን ልጃገረዷ ወደክፍልዋ ታስገባኛለች በሚል ተስፋ፣ የንፋሱን ድንፋታ ችላ ለማለት ብትሞክርም፤ ንፋሱ ግን እሷ ራሷ እሱን ፈርታ ለሁለት ቀናት ከቤት አለመውጣቷን ሲያስታውሳት ትፈራው ጀምራለች፡፡

ንፋሱ ዛፎችን ከነሥራቸው ገንድሶ መጣሉን፣ ሰዎች ከየመንገዱ ማባረሩንና እንስሳት ማስደንበሩን እየነገራት ሃይሉን እንድታውቀው ያደርጋል፤ እሷ ግን

እየተለመጠች በመደበቅ ህይወቷን ለማጥፋት ተቸግሮ ጤንነቷን ብቻ በመጉዳት ላይ መሆኑን ይነግራታል፡፡

አበባዋ ግን በህይወቷ የምትመኛቸውን ነገሮች ላትፈፅም ባትሞት ምኞቷ ነው፡፡ በልጃገረዲቷ ፀጉር መሐል ተሰክታ ለአንዲት ቀን ውብ ልታደርጋት ወይም በአደባባይ ተተክላ የሚመለከታትን ደስ ለማሰኘትና ንቦች ሲሰፍሩባት ለማየት እንደምትጓጓ ሁሉ አልደበቀችውም፡፡

አበባዋ በአፈታሪክ ሲነገር እንደሰማችው ንፋሱ ማሞን ከምትባል ደሴት የመጣ ሲሆን፣ ማሞን ደግሞ ሞደስ የሚባል ንጉስ ይገዛት ነበር፡፡ እዚያ ያሉ አበቦች ደግሞ፣ ንጉሱ ከየአገሩ የሰበሰባቸውና እሱን ለማግባት ፍቃደኛ የሆነች ልጃገረድ በመጥፋቷ፣ የእምቢ ባይ ደናግሎችን ደም ተመግበው ያደጉ መሆናቸውን የሚተርክ አፈታሪክ መስማቷን ስትነግረው፣ አፈታሪኩ እውነተኛ መሆኑን ይነግራታል፡፡

ንፋሱ የመጣበትን አገር በራሱ አንደበት የሰማችው አበባም ተስፋ መቁረጥዋ እየከበደ ይመጣል፡፡ ማልቀስም ትጀምራለች፡፡

የንፋስ ጓደኛ የሆኑት በረዶና ዝናብም በእሷ እና በመሰሎቿ ላይ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡ ራስዋን ከውሽንፍሩና ከውጅንብሩ ለማዳን ብላ፣ አጠገቧ ወዳሉ አበቦች ለመደበቅ ስትሞክር፣ አበቦቹ ግን ከንፋስ ጋር ባደረግሽው ግንኙነት ራስሽን አርክሰሻል ብለው ይሸሿታል፡፡

ከንፋሱ መፀነሷንና አበባዋን ገልጣ በገዛ ፍቃዱ መደፈሯን ሲነግሯት፣ ምኞቷ በአጭር የመቅረቱ ነገር ያሳስባትና፣ ራስዋን ለማጥፋት ትፈልጋለች፡፡ በማኅፀኗም ከፋትን በማርገዟ ተፀፅታ፣ የማይረባ ዘር ከምተካ ራሴን ብገል ይሻለኛል ብላ፣ አጠገብዋ ላሉ አበቦች ከሥርዋ ውሃ ወስደው እንዲያደርቋት ትማፀናቸዋለች፣ እነሱም ይተባበርዋታል፡፡

በማግስቱ ልጃገረዷ የሞተችባትን አበባ አንስታ ሃዘኗን ስትገልፅና መሰሏን ለመተካት ከእናትዋ ጋር ስትነጋገር ታሪኩ ይጠናቀቃል፡፡

### 3.3.1.2. ትንታኔ

በዚህ አጭር ልቦለድ ውስጥ አበባዋ ሰውኛ ተደርጋ መሳሏን ብቻ ሣይሆን የቀረበችበት ዘይቤም ተምሳሌታዊ ነው፡፡ በሰውኛ ገፀ ባህርይ ለመሳሏ ብዙ ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል፡፡ አበባዋ እንደ ሰው ታፍራለች ትበሳጫለችም ‹‹… አበባዋ ጠቅላላ ሥሮቿን አጠንክራ፣ መለመኔ አይደለም፡፡ ግን አልችልም ብዬ ነው›› አለችው ብስጭት ብላ (ገፅ 120) ነፋሱም የደስታ ስሜቱን በቃላት ይገልፃል (ገፅ 120)፡፡ መረሳት ያንገበግባታል፣ ልክ እንደ ሰው ልጅ አለመታወስ ያሳስባታል (ገፅ 119) ፡፡

አበባዋ እንደ ሰው ተስፋ የማድረግና ተስፋ የመቁረጥ ባህርይ አላት፡፡ ምኞት ይገባታል፡፡ ዓላማዋ ልጃገረዷ‚ን ማስዋብ ነው እንጂ ተረስታ መቅረት አይደለም፡፡

> ‹… ውሃ ሲያጠጡኝ በነበሩ እጆቿ ትቀጥፊኝና በሚሞቁ ጣቶቿ ትይዘኛለች፡፡ ትመሰጥና ታሽተኝ ይሆናል፡፡ በመንገድ የሚያዩዋት፣ ‹ውይ ይቺ ልጅ… እንዴት የምታምር አበባ ናት› ይሏታል፡፡ የከተማው ሰዎች እሷን ተከትለው ሁሉም በየልብሶቻቸውና በየፀጉሮቻቸው አበባ ሸጉጠው በጐዳናዎች ይመላለሳሉ፡፡›› (ገፅ 118)

ይኼው ነው ህልሟ፡፡ ኖርኩኝ የምትለው ልጃገረዷቷን ምን ያህል እንዳስዋበቻት አላፊ አግዳሚው ሲመሰክር ነው፡፡ እናም ትጠብቃታለች፣ ከአሁን አሁን መጥታ ቀጥፋ ትወስደኛለች በሚል ተስፋ፡፡

ነፋሱ መኖርያውም ያልተለመደና ቁጣ የበዛው ነው፡፡ ነፋሱ ጨለማ ጉድጓድ ውስጥ ነው የሚኖረው፣ በቁጣ መዲና፡፡ ማደሪያውም መከረሚያውም ጨለማ ውስጥ ነው፡፡ ጨለማው ደግሞ ጉድጓድ አለው፡፡ ከዚህ ጉድጓድ የሚወጣው ንፋስ ነው የአበባዋን ህልውና የሚፈታተናት፡፡ ንፋሱ በድምፁ ነጐድጓዳማነት በመከረሚያው አስፈሪነት፣ በአመጣጡ ድንገቴነት ፍርሃትና ድንጋጤን የሚያስተላልፍ ነው፡፡ ንፋሱ ደግሞ ብቻውን አለመምጣቱ አበባዋን ብቻ አይደለም ፍርሃት የጫረባት፣ አበባዋን በተከለቻት ልጃገረድ ላይም ተፅዕኖ አሣድሯል፡፡

ለዚህም ነው አበባዋ እንደ አታላይ በምትቆጥረው ንፋስ የምትደፈረው፡፡ ያለ ሴቲቱ ፈቃድ ወሲብ መፈፀምም በአራዊትም ሆነ በእንስሳት ዘንድ እንደማይፈፀም

ይነገራል፡፡ በዚህ ልቦለድ ውስጥ ግን ንፋስ የመድፈር ስልጣን፣ አበባ ደግሞ የመደፈር ዕጣ ወድቆባታል፡፡ አበባዋ ፍርሃት ንጧት ስታለቅስ ማልቀሷ ንፋስን ግራ ያጋባዋል፡፡ ‹‹የሚያስለቅስሽ ምንድነው? .... ትጠይቂኝና ታለቅሺአለሽ፡፡ ንክ አበባ›› (ገፅ 1 ነ23)፡፡

> እንደገና ገላዋን አራግፋ ሌላ አንዲት ነጭ ዛላ አበባ ጣለች፡፡
>
> ‹ብነግርህ ታምነኛለህ?››
>
> ‹‹ለምን አላምንሽም?››
>
> ‹‹ውሸታም››
>
> ለቅሶዋ ጠፍቶ እንደሚሽኮረመም ልጃገረድ ፊቷን ከነፋሱ አዙራ አንገቷን ሰበር አደረገች (ገፅ 124)

ከላይ እንደተጠቀሰው በአበባ እና በንፋስ መሃከል ያለው ምልልስ በሰውኛ ዘይቤ ከመቅረቡ በተጨማሪ፣ አቀራረቡም የሰውን ልጅ ረቂቅ የስሜት መግለጫ የሆኑትን ባህርያት ለንፋስ እና ለአበባ በመስጠት ነው፡፡ ታምነኛለህ? አላምንሽም ይባባላሉ፡፡ ቃሎቻቸውን በመሃላ በማፅናት ይጥራሉ፡፡ ‹የማይተማመን ባላጋራ በየወንዙ ይማማላል› የሚለው ብሂል ለንፋስና አበባ የተነገረ ምሳሌ እስኪመስል ድረስ፡፡ ያም ሆኖ ግን የአበባ ልምምጥ ፍሬ አያፈራም፡፡ የአበባ የተለሳለሰ አንደበት የንፋስን ልቦና አያለዝብም፡፡ የምስኪኗን ድምፅ ሰምቶ ጆሮው ቃሏን ለመስማት አያዘነብልም፡፡ ለዚህም ነው አበባዋ ክብሯን የምታጣው፡፡ በጓደኞችዋ ዘንድ ደረጃዋ ዝቅ ብሎ የሚገኘው፡፡

አበባዋ ተገድዳ በመደፈርዋ ጓደኞቿ አግልለዋታል፡፡ አጠገቧ ቆሞ መገኘት የራሳቸውን ደረጃ የሚያሳንሰው መስሎ ተሰምቷቸዋል፡፡ ከንፋስ ጋር በመተኛቷን ሊቀበሏት አልወደዱም፡፡ ማህፀንሽ ውስጥ ከንፋስ የተረከብሽው ክፋት ስላለ ልትቀላቀይን አይገባም በማለት መጠቃቷን በፈቃደኝነት እንደተደረገ ብልግና ቆጥረውባታል፡፡ ለዚህም ነው የሚነክሷት፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው *በአበቦች ታሪክ* ውስጥ ያሉት ዋና ገፀ ባህርያት ሁለት ናቸው፣ አበባዋና ንፋሱ፡፡ እነዚህ ገፀባህርያት ሰውኛ ተደርገው ተቀርፀዋል፡፡ ሁለቱም የሚወክሉት እንደ ትዕምርት የሚጠቀሱ ነገሮች አላቸው፡፡ አበባዋ ውብ ናት፣ ንፁህ ናት፣ የምትኖርበት እና ልትሞትለት የምትፈልገው ዓላማ አላት፡፡

ነፋሱ ደግሞ ሃይለኛ ነው፤ በፍጥረታት ጭንቀት ሀሴት ይሸምታል፤ ለሌሎች ግድ የለውም፡፡

በሥነ ጽሑፍ ሙያተኞች ዘንድ እንደሚገለፀው አበባ እንደ ትዕምርት የሚወክለው ባህርይ ደካማ ደናግላንን ሲሆን ነፋሱ ደግሞ ሃይልን ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በቀረበው ትንታኔ መሰረት ‹የአበቦች ታሪክ› አሊጎሪነቱ ጉላ ያለ ነው፡፡ ጠንካራው፣ ወንድነት የሚሰማው፣ በማርበድበድ የሚታወቀው ፍጥረት፣ በፆታ የማትመስለውን በባህርይ የማትወዳቸውን ሴት እንዴት እንደሚጨቁናት እና ወድዳ ባላደረገችው ሩካቤ የሚደርስባትን የተሰዳጅነት መንፈስ አጉልቶ የሚያሣይ ነው፡፡[7]

## 3.3.2. *የድንች መዋስዕት*

ይህ ታሪክ *አለንጋና ምስር* በሚለው መጽሐፍ የተካተተ ነው፣ መጽሐፉ በ2000 ዓ.ም የታተመ ሲሆን፣ 17 አጫጭር ልቦለዶችን ይዟል፡፡ *የድንች መዋስዕት* ከገፅ 160-165 ላይ ይገኛል፡፡ መጀመሪያ አፅመ ታሪኩን ቀጥሎ ደግሞ ትንታኔው እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

### 3.3.2.1. አፅመ ታሪክ

‹*የድንች መዋስዕት*›፣ በወርሃ ነሐሴ፣ በአንድ አትክልት ሥፍራ ተሰባስበው ስለራሳቸው እና ስለ መሰሎቻቸው ዝማሬ የሚያስደምጡ ድንቾች የሚተርክ አጭር ታሪክ ነው፡፡ ድንቾቹ ጓደኞቻቸው ከነሱ ተነጥለው በመወሰዳቸው እንደ ዕድለኛ ይቆጥሯቸዋል፡፡ ድንቾቹ በሰው ልጅ የሚወሰዱትና ከመሃከላቸው የሚነጠሉት በተወካዮቻቸው ነው፣ ተነቅለው የሚወሰዱት በሰው ለመበላት ነው፡፡ ይህንን መበላት እንደ ጣፋጭ ሞት፣ እንደ ተፈላጊ ዕጣ ፈንታ በመቁጠር ፣ ቀድመዋቸው በተወሰዱ በጓደኞቻቸው መንፈሣዊ ቅናት ያድርባቸዋል፡፡

---

[7] Baldic Chris (2001) የፃፈውን The Concise Oxford Dictionary of Literary Terms የሚለውን መጽሐፍ ልብ ይሏል?

ከድንቾቹ መሃከል አንድ አረንጓዴ ከለር ያለው ድንች አለ፡፡ ይህ ድንች ራሱን ከሌሎች ያገለለ ነው፡፡ በመዝሙራቸው ውስጥ ድምፁን አያሳትፍም፣ በውይይታቸው ውስጥ ሃሳቡን አይቀላቅልም፤ ዝም ብሎ በመኮለት ያውቁታል፡፡ ድባቴውን ለማስለቀቅ በብዙ ይጥራሉ፡፡ እነሱን መስሎ ባለመገኘቱ ጆሮው አጠገብ መጥተው ይጮሁበታል፡፡ በስድብ ያንጓጥጡታል፡፡ እሱ ግን በዝምታው ይቀጥላል፡፡ እነሱም ድንቹን ከነድባቴው ትተውት ዝማሬያቸውን ይቀጥላሉ፡፡

ዝማሬው ከቀጠለ ከሁለት ሣምንታት በኋላ ድንቾቹን የዘሩዋቸው ገበሬዎች የሣጠራ ዕቃዎችን ዶማዎቻቸውን ይዘው ይጠጉዋቸዋል፡፡ የተከሉዋቸው ገበሬዎች ሊነቅሉዋቸው ሲመጡ፤ ድንቾቹ ተልዕኮአችንን ፈፅመናል፤ ለዚህም ነው የተመረጥነው በሚል ስሜት፤ ዕልልታና ሣቅ ለማሰማት ዝግጁ ይሆናሉ፡፡

ገበሬዎቹ ዶማዎቻቸውን ወደ ማሣ አስጠግተው መቆፈር ሲጀምሩ፤ ድንቾቹ እየተሽቀዳደሙ፤ ለገበሬዎቹ ፈቃድ ለመገዛት ከአፈር ለመውጣት ይጣደፋሉ፤ አቅም አንሷቸው አሊያም ገበሬዎቹ ሳይጠጓቸው ቀርቶ ያልወጡት ድንቾች ደግሞ የዶማው መዘግየት ያሳስባቸዋል፡፡ የናፈቁት ሞት እነሱን የሚያገኝበት ጊዜ እንዳይራዘም ይፀልያሉ፤ ፈጣሪያቸውን ይማፀናሉ፡፡

ከገበሬዎቹ መሃል አንዱ፤ ከመረጣቸው ድንቾች አንደኛው አረንጓዴ መልክ ያለው ነበርና አሽቀንጥሮ ይወረውረውና ከመሰሎቹ ይለየዋል፡፡ አረንጓዴው ድንችም ሞትን በማምለጡ ደስተኛ ይሆናል፡፡ ቀደም ሲል ጓደኞቹ በመዝሙራቸው መሃል እሱን ተርበው ቢያንጓጥጡትም፤ እነሱ በሣጠራ ከተከተቱ በኋላ እሱ በተራው ለመሞት አልተፈጠርኩም ብሎ ሲዘምር እናደምጠዋለን፡፡ ይኼ፤ በመልክም በባህርይውም ልዩ የሆነው ይህ ድንች ልጅ ምኞት «መቀቀል» ፍላጎቱ አይደለም፡፡ ራሱን ጠብቆ፤ እርጅናውን አይቶ፤ ሠማይና ምድር ሲያልፍ የማየት ራዕይ አለው፡፡ ሞት ወደ ማይደርስባቸው አካባቢዎች ተሽሎክሉኮ መሄድ ሲጀምር፤ አንዲት ነጋዴ አግኝታው፤ ከያዘቻቸው ድንቾች ጋር ቀላቅላ ልትሸጠው ዘንቢልዋ ውስጥ ትከተዋለች፡፡ ዘንቢሉ ውስጥ ያሉ ድንቾች፤ ይኼ ቀደም ሲል ተወርውሮ የነበረው ድንች ባለመሞቱ ቅር ተሰኝተውና በብቸኝነቱ ተከፍቶ እንደተቀላቀላቸው

በመቁጠር አቀባበል ያደርጉለታል፡፡ በንፅህና ጉድለቱ ምክንያት ከመሃከላቸው እንዳይነጥሉት በመፍራት የገላውን ጭቃ ያጠሩለታል፡፡

ሴትየዋም ገበያ ሂዳ ከደረደረቻቸው መደቦች መሃል በአንዱ ስር ትሸጉጠዋለች፡፡ አረንጓዴው ድንች ከላይ የተጫኑት ድንቾች እንደ ከበዱት ቢናገርም ለመስዋዕትነት እንጂ ለድሪያ እንዳልተጠሩ ይነግሩታል፡፡ እሱ በመሞት አያምንም፤ እነሱ ግን መጪው ትውልድ እንዲከተላቸው መሞት ግድ እንደሆነ ይነግሩታል፡፡

በመጨረሻም ራሱን ከነሱ ነጥሎ፤ መደቡን አፍርሶ፤ ፊት ለፊት ወዳገኘው ቦይ ሲቀላቀል፤ ድንች ነጋዴዋ ልትከተለው ብላ መልሳ ደግሞ አለመብሰሉን አስባ ተወችው፡፡ ቦዩም አረንጓዴውን ድንች ይዞ ከድንጋይና ከቆሻሻ ጋር ይዞት ይወርዳል፡፡ ብዙ አባጣ ጉርባጣ የሆኑ የሕይወት መንገዶችን ይጓዛል፡፡ በመጨረሻም ሞት ከንዱን ጨብጦ ይዞት ለጀርት ሆድ ይዳረጋል፤ እየጮኸም ይበላል፡፡

## 3.3.2.2. ትንታኔ

በ‹የድንች መዋስዕት› አጭር ትረካ ውስጥ ያሉ ድንቾች፤ እንደማንኛውም አሊጎሪያዊ ሥነ ጽሁፍ ሰውኛ ተደርገው ተቀርፀዋል፡፡ ልክ እንደ ሰብዐዊ ፍጡራን ሃይማኖት አላቸው፤ ይፆማሉ ይፀልያሉ፡፡ ቅዱስ መጽሐፍም አላቸው፤ መፃዒ እድላቸው የተፃፈበት፤ ምኞት ህልማቸው የሰፈረበት፡፡ ይህ ባህርይ ደግሞ በሰማይ ለሚበሩም ሆነ በምድር ለሚሽከረከሩ ፍጥረታት የተሰጠ አይደለም፡፡ በልቦለዱ ውስጥ የምናገኛቸው ድንቾች የሚያደርጉት መፆም መፀለዩ፤ በሃይማኖት አንቀልባ መታዘሉ ለሰው ልጅ የተቸረ ፀጋ እንጂ በሁሉም ፍጥረታት ላይ የወረደ ልማድ አይደለም፡፡

ደራሲው ወይም ተራኪው ከድንቾቹ ቅዱስ መጽሐፍ ጠቅሶ፤ እንደ መግቢያ ብሎ ካሰፈረው አንቀፅ እንደምንረዳው፤ ደንቾቹ ለራሳቸው ልዩ ግምት አላቸው፡፡ ሞትን በፍራትና በስጋት ሳይሆን በእቅፉ ስር ለመዋል ሲጣደፉ ነው የሚታዩት፡፡ ራሳቸውን ለአንድ ታላቅ ዓላማ አጭተውታል፡፡ ይህ ታላቅ ዓላማ በፈጣሪ ዘንድ የተጣለባቸውን ሃላፊነት እንጂ በራስ ተነሣሽነት የልቦናን ፈቃድ በመከተል ብቻ

የተመሠረተ አይደለም፡፡ ቀድሞ ነገር ዓላማ ነው ሰውን ሰው ካደረጉት ነገሮች አንዱ፡፡ ሰው ነው አንድ ነገር ለመሆን ወይም አንድ ቦታ ለመድረስ ዋጋ የሚከፍለው፡፡ ዓላማ ያለው ሰው ርዕይ አለው፡፡ የርዕይ ባለቤት ደግሞ ሰው ነው እንጂ እንስሳት አይደሉም፣ አራዊት አይደለም፣ እፅዋትና አዝርዕት አይደሉም፡፡ ዓላማ ከአሁን በኋላ የሚሆን ነው በአብዛኛው፡፡ በልቦለዱ ውስጥ ግን ድንቾቹ ዓላማ አላቸው፡፡

በአማኒያኑ ድንቾች ዘንድ ሞት ቅዱስ ነው፣ ሞት ራስን ለአንድ ታላቅ ዓላማ ዝግጁ ማድረጊያ ስልት ነው፡፡ ሞታቸው ለሰው ልጅ ተብሎ የሚከፈል ሰማዕትነት ነው፡፡

ድንቾቹ ለሞት የሚታጩት፣ ሞታቸውን በናፍቆት የሚጠባበቁት፣ በወርሃ ነሐሴ ነው፡፡ በርግጥም ወቅታቸው ነው፣ በስለዋል ደርሰዋል ተብለው ለገበታ የሚታደሙት፡፡

*በየድንች መዋስዕት* ውስጥ ያሉ ገፀ ባህሪያት አሊጎሪ ናቸው ብለን አምነን እንድንቀባላቸው የሚያደርገን ብዙ ምክንያቶች አሉ - እንደ ሰው ልጅ በፈጣሪ ላይ ያላቸው እምነት የፀና ከመሆኑ በተጨማሪ፣ እንደ ሰው ልጅ በትንቢት የተነገረላቸውን ሕይወት ለመኖር ከመፍጨርጨራቸው በተጨማሪ፣ ድንቾቹ ስሜታቸውን ዜማ አልብሰው በግጥም አዋህደው የማቅረባቸው ምስጢርም፣ ላይ ላዩን ስለ ድንች ያወራሉ እንጂ ውስጥ ውስጡን ግን ድንቾቹ ሰዎች ናቸው፡፡ ድንቾቹ ስለሚኖሩለትም ሆነ ስለሚሞቱለት ህይወት በቅጡ የሚያውቁ ሰዎችን ለመወከል የቀረቡ ናቸው፡፡

ሕብረ ዜማ (1) ‹‹የዘሩን እየመጡ ናቸው
በዶማና በእጆቻቸው
ተልእኮአችንን ሊቸሩን››

ሕብረ ዜማ (2) ‹‹ይሔን በዳንኪራ፣
ይሔን በከበሮ፣
ይሔንን በክራር፣
ይሔንን በዋሽንት፣
በዕልልታና በጣቅ ካልተቀባበልነው፣
ዓላማችን ሁሉ እንደተረሳ ነው፡፡›› (ገፅ 165)

ድንቾቹ ከነሱ ቀደም ብለው፣ በገበሬዎቻቸው ተመርጠው የመነቀል ዕጣ ባገኛቸው ድንቾች እጅጉን ይቀናሉ፣ ዕድለኞች ናቸው ሊበሉ ነው ይላሉ። እነዚህ ድንቾች - እነዚህ በድንች ተመስለው የቀረቡት ድንቾች - በገዛ ፍቃዳቸው አይደለም ሞታቸውን የሚሞቱት። የበላይ አላቸው። ገበሬ ነው የተከላቸው። ገበሬው ፈጣሪያቸው ነው። በህይወት እንዲኖሩ እንዳደረገ ሁሉ በሞትም ከዚህ አለም ሊለያቸው ይችላል። ገበሬው ለእያንዳንዱ በድንች ለተመሰለው ሰው ቀን አለው። ፈጣሪ ነውና በፈጠራቸው ድንቾች ላይ መሰልጠን ይወዳል።

ከነዚህ ድንቾች ጋር ሕብረት የሌለው አንድ ሌላ ድንች አለ። ድንቹ ከፊል ጐኑ አረንጓዴ ነው፣ ከመሰሎቹ ብቻውን በስሎ ባለመገኘት ይለያል። በዘፈናቸው ውስጥ ድምፁ የለም፣ በግጥሞቻቸው ውስጥ የራሱ ስንኝ የለም። ይህም በእሱ ጥሩ እንዳይሰማቸው አድርጓል፣ በዚህም የተነሣ አግልለውታል።

መገለሉ አላስደነገጠውም፣ ከማኅበራቸው ተነጥሎ መዋሉ አላስበረገገውም። አረንጓዴው ድንች በአቋሙ የሚፀና ነው። አረንጓዴነቱ ጠቅሞታል። ከመሰሎቹ የተለየ ቀለም ስለተፈጠረለት ደስተኛ ነው። ያልተለመደ ቀለሙ በአቋሙ እንዲፀና አግዞታል።

ደራሲው ወይም ተራኪው የድንቹን አረንጓዴ መሆን መግለጽ የፈለገበት ምክንያት የተናቀነቱን ለመግለፅ ነው። ሌሎች አረንጓዴ ቀለም አልለበሱም፣ ይኼኛው አለመብሰሉ የሚገለጥበት በለበሰው ቀለም ነው። ተራኪው ቃል በቃል ገና በቅጡ ያልበሰለ (ገፅ 164) ይለዋል። ይደብረዋል፣ ግልምጫ አይፈታተነውም፣ አውሬ ብለው በዜማ ቢሰድቡትና ባለመዘመሩ ቢኮንኑትም ግድ የለውም።

የገበሬዎቹ ዶማ የዘገየባቸው ድንቾች ራሳቸውን ለሰው ልጅ ሆድ አሳልፈው ባለመስጠታቸው ይኮንናሉ። ለእነሱ ሞት ቢዘገይ እንጂ አይቀርም። በአጠቃላይ ትረካው ገፀባህርያቱን ሰውኛ በማድረግ ረቂቅ ባህርያት እንዲንፀባረቅባቸው አድርጓል። ድንቾቹ የሰውን ልጅ ባህርይ ማዕከል ያደረጉ ናቸው። ድንችን በሰው ልጅ መስሎ ሲያቀርበው፣ የአረንጓዴ ድንች ውክልና ደግሞ፣ ከመሰሎቻቸው አፈንግጠው የሚወጡ እና ከተልዕኮአቸው የሚያፈገፍጉ፣ በተፈጥሮአቸው

ያደረባቸውን አንዳች ጉድለት መመኪያ በማድረግ ለአላማቸው ከሞት ይልቅ ወደ ኋላ የሚሉ ግለሰቦችን የሚወክል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

## 3.4. አሊጎሪ በአሣምነው ባረጋ አጭር ትረካ ውስጥ

የአራዳው ወንበር በአሣምነው ባረጋ በተደረሰውና ‹የትሮይ ፈረስ እና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች› በሚለው መጽሐፉ ላይ የተካተተ አጭር ትረካ ነው፡፡ መጽሐፉ በ1994 ዓ.ም የታተመ ሲሆን፣ በውስጡ 11 አጫጭር ልቦለዶችን ይዟል፡፡

### 3.4.1. *የአራዳው ወንበር*

*የአራዳው ወንበር* የሚለው አጭር ልቦለድ የትሮይ ፈረስ ለሚለው መድበል ውስጥ ከተካተቱ ልቦለዶች አንዱ ሲሆን፣ ከገፅ 179-202 ባሉት ገጾች የሚገኝና በ1986 ዓ.ም የተፃፈ ድርሰት ነው፡፡ መጀመሪያ አፅመ ታሪኩን ቀጥሎ ደግሞ ትንታኔው እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

#### 3.4.1.1. አፅመ ታሪክ

*የአራዳው ወንበር* ፥ አዲስ አበባ፥ ፒያሣ እምብርት ላይ በሚገኝ አንድ ካፌ ውስጥ አገልግሎት ስለሚሰጥና ወደካፌው ስለሚገቡና ስለሚወጡ ተስተናጋጆች የሚያወጋ የአንድ ወንበር አጭር ታሪክ ነው፡፡

ልቦለዱ በአንደኛ መደብ ተራኪ የቀረበ ነው፡፡ ወንበሩ የራሱን የትመጣነት ብቻ ሳይሆን ወደካፌው ስለሚዘልቁትና ራሱ ላይ ስለሚቀመጡበት ሰዎች የሚያውቀውን ያህል ይተርካል፡፡ ወንበሩ በጥድ ዛፍ የተበጀ ሲሆን፣ በቁመትም ሆነ በግዝፈት ተወዳዳሪ ባልነበረው ዘመን፣ አንድ የነጋዴ ምሣር ያለዕድሜው ቀጭቶት ለወንበርነት እንዳበቃውና ከመሰሎቹ የመለየት ዕጣ ፈንታ እንደወደቀበት ይናገራል፡፡

ወንበሩ፥ ጠዋት በተለመደ ሰዓት፣ ወተት ይዘው የሚመጡትን አሮጊት አለባበስ፣ አነጋገርና ባህርይ ምን እንደሚመስል ይተርካል፡፡ ከባሬስታው ጋር የሚያደርጉትን ጭውውት ሰምቶም፣ አሮጊቷ ለከፋ ድህነት ለመጋለጥ የበቁት የሚጠራቸው ሰው

በአጠገባቸው ስለሌለና የአብራካቸው ክፋይ የሆነ ልጅ ለማፍራት ባለመታደላቸው መሆኑን ይገነዘባል፡፡ በዛፍ ዘር እንዲህ ዓይነቱ ሀብታም እና ደሀ የሚባል ጐራ ባለመኖሩ የፈጠረውን የፅድ አምላክ ያመሰግናል፤ የሰው ልጅ አስተዳደርንም ይተቻል፡፡

ወንበሩ÷ ማታ አልኮሆል ሲጠጡ ያደሩ ሁሉ ጠዋት ወደካፌው ገብተው ቡና የመጐንጨትና ሲጋራ የማቡነን ልምድ እንዳላቸው አጢኗል፡፡ ከእነዚህ ልማደኞች አንዱ የሆነው ደላላው በሻህ ወደ ካፌው ገብቶ ተራኪው ወንበር ላይ ተቀምጦ የቀጠረውን ባለጉዳይ እየተጠባበቀ ሳለ ባለጉዳዩ የካፌውን ደጅ ዘልቀው ይገባሉ፡፡ ወንበሩ የባለጉዳዩ ግዙፍ መሆን አይቶ እንዳይቀመጡበት ወደፈጣሪው ቢማፀንም፤ ደላላው ወንበሩን ለኚህ ግዙፍ ሰው በመልቀቁ የፈራው ነገር ደርሶበት ሰቆቃው የበዛ ይሆናል፡፡

በማግስቱም በዚያ ግዙፍ ሰው ምክንያት ሰውነቱ ቢዝልም፤ እንደምንም ተበራትቶ ሥራውን ይቀጥላል፡፡ ሁለት ወጣት ፍቅረኛሞችም ወንበሩ ወዳለበት ቦታ ይቀርቡና ይህንን ወንበር ስለመረጠችው ትቀመጥበታለች፡፡ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ አብሯት ያለው ፍቅረኛዋ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ጥሏት ወደሌላ አገር እንዳይሄድ ስትለምነው ይሰማል፡፡

እንደዚያም ሆኖ፤ ብዙ ባለጉዳዮችን ቢያስተናግድም፤ አንድ ከበድ ያለ ሰውነት ያለው ሰው ከተቀመጠበት በኋላ ህመምና እርጅና እየተጫነው ሄደ.ል፡፡

በሌላ ቀን ደግሞ በሻህ ሌላ የሙያው ባልደረባውን አስከትሎ ወደወንበሩ ሲጠጋ፤ ወንበሩ ከዚህ ቀደም በወፍራሙ ተስተናጋጅ የደረሰበትን ቅጣት አልዘነጋም ነበርና ቂም ቋጥሮ የበቀል ርምጃ መውሰጃ መንገድ አጠንጥኖ ጠበቀው፡፡ ወንበሩ እንደዛተ ብቻ አልቀረም፤ ዙሪያው የተሰገሰጉት ሚስማሮች ሹል ጫፍ ሽቅብ እየገፋ የደላላውን ሱሪ ቦትርፎ መጣቂያ ያደርገዋል፡፡

የደላላው ሱሪ ከተቦተረፈ በኋላ ስሜቱ ይታወካል፤ መነጫነጭ ይጀምራል፤ ሥራውንም ተረጋግቶ የመሥራት አቅም ያጣል፡፡

3.4.1.2. ትንታኔ

የአራዳው ወንበር ÷ በሰውኛ ዘይቤ በመቅረቡ ልክ እንደ ሰው ልጅ ለፈጣሪው ፀሎት ያደርሳል፣ ‹አማን ያሳደርከኝ አማን አውለኝ› ብሎ፣ ለመኖር እንቅፋት የሆኑበትን ያጠፋለት ዘንድ ጸሎት ያደርሳል፣ ‹ስጋ የከበደውን አርቅልኝ› ብሎ (ገፅ 180)፡፡

‹የአራዳው ወንበር›፣ እንድ ጉልማሳ ስለ ወጣትነት የውበት ዘመኑ የሚተርክ እስኪመስለን ድረስ፣ ራሱን ‹ሰውኛ› ባህርይ አላብሶ ያስተዋውቀናል፡፡

> ‹... ዛሬ እንዲህ ተቀለጣጥሜ ብታዩኝ! ሸበላ የጥድ ዛፍ ነበርኩ፡፡ በእውነት! ከጥድ ቆነጃጅት እኔን ስታይ የማትሽኮረመምና ቅጠሏ የማይርገበገብ አንድ ስንኳ አልነበረችም! ዕልፍ የጉሬዛ÷ የጦጣ የዝንጀሮ፣ የንስር ... ቤተሰብ ሰብስቤ የማሳድር ጉበዝ! (ገፅ 179)፡፡

የአራዳው ወንበር፣ ፈጣሪ ባደረገላትና እያደረገላት ባለው ነገር እጅጉን ደስተኛና አመስጋኝ ነው፡፡ ‹...የሞቱ ቅጠሎቼን ንፋሱ ያነሳልኛል፡፡ ያደፈ ገላዬን ዝናቡ ያጠራልኛል፡፡ የተጨነቀ መንፈሴን የእፅዋት የማለዳ ዜማ ያሰክንልኛል...› (ገፅ 179)

ወንበሩ የሰዎችን ቋንቋ ያዳምጣል፡፡ ሹክሹክታቸውን ይጋራል፡፡ አሮጊቷ ወደካፌው ገብተው ለራሳቸው እርቦኛል ሲሉ ወንበሩ ግን ለራሱ የሚያንሾካሽኩለት ይመስለዋል፡፡

ወደካፌው የሚገቡትን ሰዎች የኑሮ ደረጃ እያየ ይገረማል፡፡ በደሀና በሀብታም መካከል ስላለው የኑሮ ልዩነት ይተክዛል፡፡ በዕፅዋት ዘንድ ግን ‹ለማኝ ተለማኝ የሚባል ነገር የለብንም› ብሎ (181) ዕጣ ፈንታውንም ያመሰግናል፣ ‹በተክሎች መሀከል ራሱን ከልሎ ሊላውን የሚያባርር ሆዳም› ባለመኖሩ ፡፡ (ገፅ 181)

የአራዳው ወንበር÷ ለወንበርነት በመመረጡ ደስተኛ አይደለም፡፡ ካፌ ውስጥ ተጐልቶ በየሰዐቱ የሚገቡ የሚወጡትን በማስተናገዱ በየደቂቃው ያጉረመርማል፡፡ የልጅነት መልኬ ተበላሸ የሚለው አንድ ተስተናጋጅ ሻይ አፍስሶበት ነው፡፡ ተስተናጋጆች፣ ስለ ወንበሩ ሕመም አይጨነቁም፡፡ ለምሳሌ አንድ ተስተናጋጅ/ የሚፋጅ ቡናና ሻይ ጠጥቶ ያለቀች ሲጋራውን ግራ ጭኑ ላይ አፋትጐ ሲያከስመው

እንደ ሰው ነው ስቃዩ፣ ኡኡታው፡፡ ‹... ፍሙ መላ ሰውነቴን ጠልቆ አቃጠለኝ፡፡ ጨስኩ፡፡ እሪ አልኩ› (ገፅ 182) በዚህና ይህንን በመሳሰሉ ብሶቶቹ የተነሣ የአንድ ደሀ ጐመን እራት አብስሎ አመድ ሆኖ ማረፍን ይመኛል፡፡

የዝሆን አካል ያላቸው አንድ ተስተናጋጅ ሲቀመጡበት ያሰማው እሪታ እና ያፈሰሰው እንባ፣ ከደረቅ እንጨት የሚፈልቅ አይደለም፡፡ ወንበሩ ልክ እንደ ሰው ነው፣ የስቃይ ዕንባው በደረቁ አጥንቶቹ መሀል የፈሰሰው፣ ወገቡ የተብረከረከው፡፡ ኧረ እንዴት ያለፍዳ ነው እናንተ! ሰውን ምን ነካው! የሰንጋ ሽንጥ በየጥዋቱ እየደረበ ተሸከመኝ ይለኛል እንዴ?› (ገፅ 185)

የአራዳው ወንበር፣ በራሱ ላይ የሚደርሱት ሀዘንና ሰቆቃ ብቻ ሳይሆን ደስታ የሚመግቡት ተስተናጋጆችንም ያስተዋውቀናል፡፡ ለምሳሌ አንዷት÷ እንደሱ አገላለፅ ‹በጥርሶቿ መሀል ብዙ ደማቅ ጨረቃዎች የሸሸገች የምትመስል› ሴት ስትመጣበት፣ ‹ለስላሳ ታፋዋ ገላዬን ሲነካው ደረቁ አንጀቴ ድረስ ነው ዘልቆ ያራሰኝ፡፡ ተፈወስኩ፡፡› ይላል (ገፅ 187) ፡፡

ያም ሆኖ ግን እርጅና እጅጉን እየተጫጫነው ስለመጣ የቤቱ ባለቤት እንኳን ከሳሎን ወደ ጓሮ እንዲጣል ያሳስብ ጀምሯል፡፡ ይህም እጅግ አሳዝኖታል፡፡ ‹... ውለታቢስ! በኔ ጫንቃ ነው እኮ ይህን ሁሉ ሀብትና ንብረት ያፈራው፡፡ ሲሆን ግምጃ ጨርቅ አልብሶ በክብር እየተንከባከበ ሊጦረኝ ሲገባው፣ መጋዘን ተጥዬ የአይጥና የሸረሪት መጫወቻ እንድሆን ይፈርዳል?› (ገፅ 191) ፡፡

የአራዳው ወንበር ቀስ በቀስ ቂም መቋጠርና በደል የፈፀመበትን ተስተናጋጅ ይበቀል ይጀምራል፣ ልክ እንደ ሰው ልጅ፡፡ ዙሪያው የተሰገሰጉ አዳዲስ ሚስማሮችን በመጠቀም ‹... በልኩ የሞተ ፈረንጅ አፈላልጐ ከኮልፌ የገዛው ከሱፍ ጨርቅ የተሰራ ሳልቫጅ ሱሪው መቀመጫ አካባቢ ሁለት ትላልቅ የዱር ዓይጦች የሚያሾልክ ቀዳዳ› አበጀለት (ገፅ 198)፡፡

በአጠቃላይ ከላይ እንደተጠቀሰው የአራዳው ወንበር፣ የማይናገረውን ግዑዝ ፍጥረት በማናገር ሰውኛ ተደርጓል፡፡ ወንበሩ እንደ ትዕምርት ዙፋኑን ሥልጣንን ይወክላልና የሚቀመጡበትን ባለስልጣኖች ባህርይ ነው የሚተችልን፡፡ ለሰው ልጅ ብቻ የተሰጡ

እንደ መሣቅ፣ ማልቀስ፣ መብሸቅ፣ መፀለይ፣ ለራስ ዋጋ መስጠት፣ ትናንትን መተረክና የበቀል እርምጃ መውሰድን አሣይቶ፣ ለአዳም ዘር ብቻ ሣይሆን ለምንገለገልባቸውና ለሚያገለግሉን ግዑዝ አካላት ፍትህ እንድንጨነቅ፣ ለየነገሮች ሚዛናዊ አመለካከት እንዲኖረን የሚያደርግ ሞራላዊ አሊጎሪያዊ ታሪክ ነው፡፡

## 3.5 አሊጐሪ በአለማየሁ ገበየሁ አጭር ትረካ ውስጥ

*አስቻኳይ ጉባኤ* ÷ ‹የአበሻ ፊት› በተሰኘው መድበል ውስጥ የሚገኝ አጭር ትረካ ሲሆን፣ በ1998 ዓ.ም በአለማየሁ ገበየሁ ተደርሶ ለንባብ የበቃ የአጫጭር ልብወለዶችና ምናባዊ ወጐች ስብስብ መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፉ 5 አጫጭር ልብወለዶችና 10 ምናባዊ ወጐች አሉት፡፡

### 3.5.1. *አስቸኳይ ጉባኤ*

ከልብወለዶቹ መካከል *አስቸኳይ ጉባኤ* የተሰኘው ትረካ ለእዚህ ጥናት ከተመረጡት ሥራዎች አንዱ ሲሆን ከገፅ 75 -88 ባሉ ገጾች የሚገኝ ነው፡፡ መጀመሪያ አፅመ ታሪኩን ቀጥሎ ደግሞ ትንታኔው እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

#### 3.5.1.1 አፅመ ታሪክ

ትረካው ለአስቸኳይ ጉባኤ በአንድ አዳራሽ ውስጥ እንዲታደሙ ስለተደረጉ የዓመቱ ወራት የሚተርክ ሲሆን፣ ጉባኤው እንዲካሄድ አስቸኳይ ጥሪ ያስተላለፈው ደግሞ ነሐሴ ነው፡፡ የስብሰባው አዳራሽ ጠባብ ሲሆን የጭቃ ግድግዳው ስለረገፈ ቤቱ ንፋስ ያስገባል፡፡

ሰብሳቢዎቹ ሐምሌና ነሐሴ ናቸው፡፡ የስብሰባው ዋና ዓላማም በብዙ መልኩ መብታችንን ረግጧል ብለው የሚያምኑበትን የሰውን ልጅ ሥርዓት ለማስያዝ እና በማኅበር ተደራጅተው መብታቸውን ለማስከበር መሆኑን አስረግጠው ለመናገር ነው፡፡

ይህንን የመብት መረገጥም በምሳሌ ሲያስረዱም የሰው ልጅ ከወሮቹ ጋር አያይዞ የሚናገራቸው አባባሎችን ይጠቅሳሉ፡፡ ያለነሱ ፍቃድና አስተያየት ‹ጥር የልጃገረድ

ጠር› መባሉ፣ ግንቦት እንደ ወረ መተት መቆጠሩ ቀልደኛ ገበሬ በሰኔ ይሞታል መባሉ፣ የጥቅምት ብርድ ቆማጣ እንደሚያስታቅፍ መነገሩ አግባብ አለመሆኑን ሰብሳቢዎቹ ያሳስባሉ፡፡

ጳግሜ ግን ይህንን ሃሣብ እጅጉን ትቃወማለች፡፡ ወራት ያለ ሰው፣ ሰው ያለ ወራት ግንጥል ጌጥ መሆናቸውን አስረድታ፣ የማኅበሩን አስፈላጊነት ትቃወማለች፡፡ ተቃውሞዋ ግን በየካቲት ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ከጉደሎ ወር የመነጨ ጉደሎ ሃሣብ ብሎ ያጣጥለዋል፡፡

ወራቱን በሃላፊነት የሰበሰበው ነሐሴም የየካቲትን ሃሣብ ደግፎ፣ ቁንፅል ቀናት ይዛ፣ እንደ ሣምንት መቆጠር እንጂ ወራትን ወክላ ለስብሰባ መታደሚ አግባብ እንዳልሆነ ቢናገርም፣ ሚያዝያ ግን ሃሳቡን እጅግ ያስቆጣዋል፡፡ በአናሣ ወራት ላይ ጡንቻን ለማሣየት የሚደረግ ሙከራ ይለዋል፡፡

ጥቅምትና ህዳር፣ የነሐሴን አብዝቶ ተናጋሪ መሆን እና ሃላፊነቱን ወስዶ ስብሰባ ለመጥራት መነሳሳቱ ሥልጣን ፍለጋ መሆኑን ጠርጥረዋል፡፡ ነሐሴም የትግል ምዕራፍ ከመከፈቱ በፊት ማኅበራቸውን የሚመሩ ጠንካራ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት እንዲመረጥ እና የተመረጡት አባላት መተዳደሪያ ህገ ደንብ እንዲያረቁ መፈለጉን ለጉባኤተኛው ያስረዳል፡፡

ይህንን ሃሣብ በመቀበልም ሰኔ ሃሣብ አቀረበ፡፡ የሚመሰረተው ኮሚቴ አራት አባሎች እንዲኖሩት እና ከአራቱ ሁለቱ ሐምሌና ነሐሴ እንዲሆኑ፣ ሁለቱን ደግሞ መምረጥ እንደሚቻል ተናገረ፡፡ ይህን ሃሣቡን የደገፉት ቢኖሩም በመስከረም ዘንድ ግን ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የድምፅ መስጫ ሳጥን ተሰናድቶ ሁሉም ወር የሚፈልገውን እንዲመርጥ ዕድሉ እንዲመቻችለት ቢያሳስብም ነሐሴ ግን የመስከረምን ሃሣብ ያጣጥልበታል፡፡

ሚያዝያም ለኮሚቴው እመጥናለሁ የሚል ወሬ ራሡን፣ አስተዋውቆ ራሱን እጩ አድርጎ እንዲያቀርብ ሃሣብ በመሰንዘሩ፣ ሃሣቡም ተቀባይነት በማግኘቱ የካቲት ራሱን ለዕጩነት አቀረበ፡፡ በተለይ የአድዋ ድል በዐል እሱ በሚገኝበት ወር መከበሩ ለመላው አበሻ የዕድሜ ልክ የኩራት ስንቅ በመሆኑ ሊመረጥ እንደሚገባው ገለፀ፡፡

መስከረምም የውበት መለኪያ መሆኑን በማስተዋል የምረጡኝ ጥያቄውን አቀረበ፡፡ የእንቁጣጣሽና የመስቀል በዐል የሚከበርበት ወር መሆኑ ዝናብና ፀሃይ አመጣጥና ማስተናገዱ ከሌሎች የተለየ እንደሚያደርገውም አስታወቀ፡፡ ጥር ግን መስከረም የዘመን መለወጫ ተብሎ የሚጠራው በሀበሾች ዘንድ እንጂ ፈረንጆች ‹ክሪስማስ› ብለው በታላቅ አጀብ እንደሚያከብሩት ከመናገሩም በላይ የጥምቀት በዐል እና አረፋ የሚከበርበት ወር መሆኑ ተመራጭ እንደሚያስደርገው ገለፀ፡፡ ሚያዚያም ለጥቆ የድል ቀናት ከሆኑት ውጪ የፈጣሪ የህይወትና የሞት ምሳሌ የሆኑት ስቅለትና ትንሣኤ በዓል የሚከበርበት ወር መሆኑን ገልጾ ሌሎቹን አሣንሶ ራሱን ያስተዋውቃል፡፡ ግንቦትም በበኩሉ የወራት ሊቀመንበር ተደርጐ ከተመረጠ፤ ሊያታግል የሚችል መዋቅር እንደሚያዘረጋ ከመግለፁም በላይ ሊቀመንበርነቱ ከፀደቀለት መስከረምን የሥነ ውበትና የባህል ሚኒስትር እንደሚያደርግ፣ ጥቅምትን የሥጋ ሚኒስትር፣ ህዳርን የፅዳት ሚኒስትር፣ ሐምሌን የእርሻ ሚኒስትር አድርጐ የተቀሩት ወራትን ደግሞ በኮሚሽነርነት በአምባሳደርነት ለመሾም ዝግጁ መሆኑን ቢያሳውቅም፤ በግንቦት ዘንድ ቦታ እንደሌለው የገባው ሰኔ የግንቦትን ሃሣብ ይቃወማል፡፡

ሌሎችም ተቃውሞቻቸውን አምርረው በመግለፃቸው መግባባት እማይችሉበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ፡፡ የተነሣበት ርዕሰ ጉዳይ ዘንግተናል በማለትም ሀምሌና ነሐሴ የተጣለብንን ታሪካዊ ሃላፊነት ለመወጣትና በጉባኤተኛው መካከል ያለውን ምስቅልቅል ገፅታ ለማጥራት በሚል ሰበብ የሊቀመንበርነቱን ሚና ለሌሎች ላለመስጠት ያላቸውን አቋም አሳወቁ፡፡ ሥልጣኑን በሞኖፖል ለመያዝም ሰኔ፣ ሀምሌና ነሐሴ በማድባት ላይ መሆናቸውን መስከረም በማሣወቁም፤ እነዚህ የክረምት ዝርያ ያላቸው ወራትም ሥልጣን ከተሰጣቸው ለበጋ ለመፀው እና ለበልግ ጥቅም የመታገል አቅማቸው የደከመ መሆኑን በማሳሰቡ፤ ጉባኤተኛው ሲታወክ እና ሀምሌ ከነሐሴ የቀማውን ጡሩንባ ደጋግሞ ሲነፋ ትረካው ይጠናቀቃል፡፡

### 3.5.1.2. ትንታኔ

‹አስቸኳይ ጉባኤ› ውስጥ የተካተቱት ገፀ ባህርያት ስማቸው የወራትን ስም የያዘ ቢሆንም በባህርያቸው ግን ሰውኛ ተደርገዋል፡፡ የወራቱ ውክልናም ለፖለቲከኞች ነው፡፡

ገፀ ባህርያቱ ችግሮቻቸውን ለመፍታት በጉባኤ ይታደማሉ፡፡ ጉባኤ መታደም ደግሞ የሰው ባህርይ ነው፡፡ እነዚህ ወራት ግን ‹ተረገጠብን› የሚሉት መብታቸውን ፈር ለማስያዝ ሃሣብ ይለዋወጣሉ፡፡ በሰው ባህርይ ውስጥ ተዘውትሮ የሚስተዋለው የራስን መብት የማስጠበቅ ነገር ያሳስባቸዋል፡፡ የጉባኤው ሰብሳቢ የሆነው ነሐሴ የሚጠቀምባቸው ቃላትም፤ ለሕዝብ ጥቅም ቆመናል ብለው የሚያምኑና የሚያሣምኑ ፖለቲከኞች የሚጠቀሙበት ዓይነት ነው፡፡

> ‹... እንደ እኔ እምነት ማኅበር መሰረታዊ ችግሮቻችን ለማየት ብሎም ለመፍታት የሚያስችል መሳሪያ ነው፡፡ ለምሳሌ ድርቅ በየትኛው ወራት ይበዛል? የሚከሰትበት ምክንያት በኛ በወሮች በግድየለሽነት ወይስ በመንግስትና በህብረተሰቡ እንዝህላልነት? ችግሩን ለመፍታት የኛ አስተዋጽኦ ምንድነው? የሚለውም ጥያቄ ይፈታበታል ...› (ገፅ 78) ፡፡

ጉባኤተኞቹ፥ አባላት ስለሚተዳደሩበት ህገ ደንብ ያሳስባቸዋል፡፡ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ያስችላቸው ዘንድ ስለሚከፍቱት የትግል ምዕራፍ ይወያያሉ፡፡ አባላቱን የማስተዳደር አቅም ያላቸው ሊቃነ መናብርት በሚመረጡበት ጊዜ አካሄዱ ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን አጥብቀው ይሟገታሉ፡፡ ምርጫው ድምፅ በመስጠት ቢሆን ይሻላል ወይስ ለቦታው እንመጥናለን የሚሉ ወራት ራሳቸውን አስተዋውቀው ታዳሚው በመረጣቸው ይሻላል በሚለው ሃሣብ ዙሪያ ይወያያሉ፡፡

ሆኖም ግን ወራቱ እርስ በርስ አይከባበሩም፡፡ እርስ በእርስ አይተማመኑም፡፡ አንዱ የአንዱን ንግግር ለመቀበል ይቸገራል፡፡ ንግግሮቻቸውም ሌላውን ለማሣነስ እና ራስን ለማተለቅ የሚደረግ መፍጨርጨር ይበዛዋል፡፡

እያንዳንዱ ወር፤ በውስጡ ላሉ ቀናት የሚሰጠውን ክብር ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፤ ለራሱ የሚኖረውን ክብር ለማሳደጊያ ይጠቀምበታል፡፡ ለምሳሌ በመስከረም ውስጥ የእንቁጣጣሽ በዐል እና የመስቀል በዐል ስለሚከበር፤ ጥር ደግሞ የጥምቀት በዐል በሚዘከርበት ጊዜ አርባ አራቱ ታቦት ወጥተው ደጅ በማሳደሩ፤ ሚያዚያ ደግሞ ትንሣኤ በዐልንና የአርበኞቹ መታሰቢያ ቀን የሚከበርበት ወር በመሆኑ አበክረው በመግለፅ ራሳቸውን አስበልጠው ይናገራሉ፡፡

> ‹እውነት ከእነዚህ ቁጥሮች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?› ጥቅምት ወደ ህዳር ጆሮ ተጠግቶ አንሾካሾከ፡፡

‹የእነ አጅሬ ዘር ነኝ ሊል ይሆናል› ሀዳር በዝግታ መለሰ፡፡

‹እነ አጅሬ እነማን ናቸው?› ጥቅምት እንደ አጥንት የቀጠነውን ፊቱን አሰገገ፡፡

‹የገኘ መደብ ነዋ!› ሀዳር አቅሎ መለሠ፡፡

‹አይመስለኝም› አለ ጥቅምት ጭንቅላቱን እየነቀነቀ (ገፅ 83)፡፡

እነዚህ በተምሣሌት ዘይቤ የቀረቡ ወራት በሚያስገርመው ተደንቀው ጭንቅላት የሚነቀንቁ፣ በሚያበሳጩው ተነጫንጩው ቅሬታቸውን የሚያስደምጡ ናቸው፡፡

አስቸኳይ ጉባኤ በሚለው አጭር ትረካ ውስጥ እንደ ትዕምርት የምንጠቀምበት ነገርም አለው፡፡ ይህም ትዕምርት ጡሩንባ ነው፡፡ ይህ ጡሩንባ በትረካው ውስጥ በተደጋጋሚ የሚጠቀስ ነው፡፡ ‹... ሁሉም ወራቶች ትናንት ማታ የተለፈፈውን አስቸኳይ የነሐሴ ጡሩንባ ሰምተው ነው በስብሰባው አዳራሽ የከተሙት› (ገፅ 75)፡፡ ቤቱ በድጋፍና በተቃውሞ ጉርምርምታ ተውጦ ነሐሴ ጡሩንባውን አስጮኸው (ገፅ 77)፡፡ ይኼ ነሐሴ አመቱን ሙሉ ነው እንዴ ይህን ጡሩንባ የሚይዘው? (ገፅ 78)፡፡

በትረካው ውስጥ የጡሩንባው አገልግሎት ጉባኤተኛውን አደብ ማስገዛት ነው፡፡ አዳራሽ ውስጥ ያሉት ወራት በተቃውሞ ወይም በድጋፍ መንፈስ ተሞልተው ለመግባባት ካልቻሉ ጡሩንባው ይነፋል፡፡ ይህን ጊዜ ነው አዳራሽ ፀጥታ የሚያረብበት፡፡ ጡሩንባው ደግሞ በሰብሳቢው እጅ ነው ያለው፡፡ ሰብሳቢው ነሐሴ ነው፡፡

ጡሩንባውን በሚዲያ ልንመስለው እንችላለን፡፡ በውክልና የቆመው መገናኛ ብዙሃን ነው፡፡ ሚዲያውን እንደልቡ ሊጠቀምበት የሚችለው ደግሞ ሥልጣን ያለው አካል ነው፡፡ ተሰብሳቢው ቢያምፅ፣ የስብሰባው ድባብ ቢለወጥ፣ አንድ ሃሣብ ተነስቶ የሃሣቡ ደጋፊዎች ተቃዋሚዎች ሲጫጫሁ ጡሩንባው መነፋቱ አይቀሬ ነው፡፡ ጡሩንባው አንድ ነው፡፡ ብቻውን ነው፡፡ ጡሩንባ የራሱ የሆነ ድምፅ የለውም፣ የያዘው ሰው ድምፅ/ ትንፋሽ ይፈልጋል፡፡ ሚዲያውም የተቆጣጠረውን ሰው ሃሣብ ነው የሚያስተጋባው፡፡

እስከ ትረካው መጨረሻ ድረስ ጡሩንባው ሃይል አለው፡፡ የሚንጫጩትን ፀጥ ያሰኛል፡፡ የሚያውኩትን ያረጋጋል፡፡ ከጡሩንባው ድምፅ በኋላ ግን የጡሩንባው ነፊ የሆነው ነሐሴ ሃሣብ እንጂ የሌሎች ወራት ሃሣብ አይስተናገድም፡፡

ሰኔ÷ ሐምሌና ነሐሴ ሌሎች ወራትን ጨቁነው የመግዛትና ሥልጣንን በእጃቸው የማስገባት ሃሣብ እንዳላቸው በመስከረም እንደበት ከተሰማ በኋላ ጉባኤተኛው መስማማት አልቻለም ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ነበር አዳራሹ ሁከት የተዘራበት፡፡ ይህንን ሁከት ለማስወገድ ግን ሐምሌ ነበር ‹ንዴት ካበገነው ነሐሴ ጡሩንባውን ቀምቶ ደጋግሞ› የነፋው፡፡ (ገፅ 79)

ታሪኩ የሚጠናቀቀው እንዲህ ሆኖ ነው - ጡሩንባው ከነሐሴ እጅ ወጥቶ ሐምሌ እጅ ይገባል፤ በግርግር፡፡ የሐምሌ ትንፋሽ በጡሩንባው ውስጥ ሰርጐ ገብቶ ድምፁን ያስደምጣል፡፡ ይህ ሚዲያው በሌላ ሰው እጅ መግባት መቻሉን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ምንም እንኳን በሐምሌና በነሐሴ መካከል ጠብና ክርክር የሌለ ቢመስልም ሚዲያው በግርግር በሐምሌ እጅ ገብቷል፡፡ የተለፈፈ አዋጅ ወይም የተነገረ ማስጠንቀቂያ አልነበረም፡፡

በአጠቃላይ ‹አስቸኳይ ጉባኤ› ፖለቲካዊ አሊጐሪ ነው፡፡ በታሪኩ ውስጥ የቀረቡት ወራት በምስያ ዘይቤ የተገለጹና የፖለቲከኞችን ባህርይ የተላበሱ ናቸው፡፡ ፖለቲከኞቹ ለራሳቸው ሥልጣን ሲሉ የሚያስነሱትን አመፅ ከመግለጹም በተጨማሪ ጡሩንባን እንደ ትዕምርት ተጠቅሞ፤ ሚዲያው የገኘው ፓርቲ ‹አፍ› መሆኑን የሚያሳይ ተሣላቂ አሊጐሪ ታሪክ ነው፡፡

## 3.6 ለአሊጐሪ በሚካኤል ሽፈራው አጭር ታሪክ ውስጥ

*ሐረግና ግራር÷ የወፍ ማስፈራሪያ እና ሌሎች አሥቂኝ ልቦለዶች በሚለው መድበል ውስጥ የተካተተ፤ በ2000 ዓ.ም የታተመና በሚካኤል ሺፈራው የተደረሰ መጽሐፍ ነው፡፡*

### 3.6.1 ሐረግና ግራር

የወፍ ማስፈራሪያ በውስጡ አራት ልቦለዶችን የያዘ ሲሆን፣ ‹ሐረግና ግራር› በሚል ርዕስ ቀርቦ ለዚህ ጥናት የተመረጠው አጭር ታሪክ ከገፅ 179 -198 የሚገኝ ነው፡፡ መጀመሪያ አፅመ ታሪኩን ቀጥሎ ደግሞ ትንታኔው እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

#### 3.6.1.1 አፅመ ታሪክ

ሐረግና ግራር የጥፋት ዘመን በነበረበት ዘመን የተፈፀመ እና ዛፎች በቁማቸው ሞተው በደረቅ ጥፍሮቻቸው ሰማዩን ሽቅብ ለመቧጠጥ በሚፍጨረጨሩበት ዘመን፣ ስለቀደመው የበረሃ ህይወቱ ስለሚተርክ ስለአንድ ግራር እና በብቸኝነት ዘመኑ ስላገኛት ስለአንዲት ሐረግ የሚያወራ አጭር ታሪክ ነው፡፡

ግራሩ÷ ብቻውን ሆኖ የሚተነፍሰውን ቀዝቃዛ አየር ፍለጋ ብዙ ታግሏል፡፡ መከራ ብዙ አስተምሮታል፡፡ ከደረቅ አለት ጠብታ ውሃ መጥጦ ለራሱ የማስቀረትን ጥበብ አግኝቷል፡፡ በብቸኝነቱ ሳይከፋ እና ተስፋ ሳይቆርጥ እንደ መሰሎቹ ቀልጦ ላለመቅረት ይታገላል፡፡ ለራሱ ህይወት ብቻ ሳይሆን፣ ይኼ ክፉ ዘመን አልፎ በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ የሚዘራበትን ቀን ይናፍቃል፡፡

ግራሩ ሁሉም ነገር መልካምም ሆነ ክፉ የሚሆነው ውስጣችን ስለጉዳዩ ባለው እምነት እንደሚወሰን ያምናል፡፡ የወፎቹ ዜማ ከአየሩ ላይ የጠፋው በውስጣችን ያሉ ወፎች በመሞታቸው መሆኑን፣ ወንዞቹ የደረቁትም በራሳቸው ደረቅ ነፍስ እንጂ ከውጭ በመጣ የተፈጥሮ ጠላት አለመሆኑን አምኖ ተቀብሏል፡፡ ከዐለቱ ውስጥ በስሮቹ አማካይነት በትግል ከሚያፈልቀው ጠብታ ውሃ ይልቅ ይህ እምነቱ በህይወት አፅንቶ እንዳቆየው ከልቡ ያምናል፡፡

አንድ ቀን÷ አንዲት ህይወት ብቅ ብላ በብቸኝነቱ አዝና እና ከጥላው በቀር አንድም ፍጥረት እንደሌለ ስታውቅ ማዘኗ እንደማይቀር ይገምታል፡፡ በረሃው አሸንፎ ሊጥላት ሲታገል ትምህርት ሊሰጣት እንደሚችል ተስፋ ያደርጋል፡፡ ግራሩ ዘላለማዊ ሕይወት በሚባለው አመለካከት እምነት አለው፡፡ ይህንንም በሕይወት ዘመኑ በተደጋጋሚ አይቷልና ከብዙ የብቸኝነት ዘመኑ በኋላ አንዲት ሽንጠ ረዥም

ተሳቢ ሀረግ፤ ከወይራና ከዛፎች ቀድማ ብቅ ብላ ወደ ህያዋን ዓለም ስትቀላቀል አዲስ አልሆነበትም፡፡

በአሸዋ ባህር ላይ መሬት ለመሬት ተስባ መኖሩ እንደማያዛልቃት ገብቶት፤ በራሱ ላይ ተጠምጥማ እንድትኖርና እንደወንድም ሊሆናት ፍቃዱ መሆኑን ይነግራታል፡፡ በመጨረሻው ሰዐት አግኝቷታልና ‹ተስፋዬ ነሽ› ብሎም ስም ያወጣላታል፡፡ የእሷ መገኘትም የጥንካሬ ምንጭ ሆኖት ስሮቹን ሰድዶ ከእናት ምድር ከርስ ውሃ ፍለጋ ይኳትናል፡፡

የግራሩና የሐረጉ ወዳጅነት ግን እንደ ጅምሩ እያበበ የሚሄድ አልሆነም፡፡ ሐረጓ የወንድሟን የግራር ውለታ ዘንግታ በራስዋ ትኩራራ ያዘች፡፡ ከሌሎች ቀድማ፤ መቃብር ፈንቅላ ሙታንን በመለየቷ ግብዝነቷ የበዛ ሆነ፡፡ እሷ በየጊዜው የለመለሙ ቅጠሎች ስታፈራ እሱ ግን ከተወለደች ጊዜ ጀምሮ ለውጥ አላየችበትምና ለሷ በሕይወት መኖር ያበረከተውን አስተዋፅኦ ሲተርክላት ልትቀበለው አልፈቀደችም፡፡

በዚህ የተነሣ በሁለታቸው መካከል መከፋፈል መጣ፡፡ በሐረጊቱ አነጋገር እና ለራስዋ በምትሰጠው ግምት ልቡ ክፉኛ ተነካ፡፡ እስዋን ለማኖር እና ከእሷ ጋር ፀንቶ ለመቆም በመቻሉ የማይደሰቱ ፍጥረታት ሊኖሩ እንደሚችሉ ቢነግራትም ያለ ግራር ደጋፊነት የበረሃ ሕይወትን ድል እንደምታደርግ በመናገር ሕልሙን አጣጣለችበት፡፡ ብቻዋን ለመኳዝ እና ተነጥላው ለመኖር ያላት እቅድ ሲሰማ ልቡ ክፉኛ አዘነ፡፡ እናም እየለመናት ልመናውን ችላ ብላ ሄደች፡፡ ግራሩም በዚህ ጊዜ መብረክረክ እና ሀዘን ይገባው ጀመረ፡፡

እናም የግራሩ ብቸኝነት ቀጠለ፡፡

3.6.1.2 ትንታኔ

በ‹ሐረግና ግራር› አጭር ልቦለድ ከባለታሪኮቹ ከሐረግ እና ከግራር የምናገኘው ሞራላዊ ትምህርት ከሰው ልጅ ባሕርይ እጅጉን የተቀራኘ ነው፡፡

ሐረግ ÷ ደካማ፣ ቃላት የምትሰነጥቅና የራስዋን መንገድ የምትከተል ናት፡፡ አትሰማም፤ አትስማማም፡፡ ለራሷ ያላት ክብርም ሆነ ግራርን የምትረዳበት ሁኔታ

የተንሸዋረረ ነው፡፡ ግራር ግን ፅኑ ነው፡፡ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ከሞት ለሚነሱት ያስባል፤ ለመጪው ዘመን ህይወት ይጨነቃል፡፡ የመከራ ንፋስ አያስጐነብሰውም፡፡ ‹ግራሩ የእሳት ትንፋጉን አሸንፎ ቀዝቃዛ አየር ለመተንፈስ ሲታገል ብዙ ዘመን አሳልፏል፡፡› (ገፅ 180)

ትረካው በመልካም ባህርያት እና በክፉ ባህርያት መካከል ያለውን ትግል የሚያሳይ በሰውኛ ዘይቤ የተፃፈ ነው፡፡ ሞራላዊ ትምህርቱ በእምነት የተሻለ የሆነውን ነገር ማግኘት እንችላለን ነው፡፡ ለሌላው ስለመኖር ነው ግራሩ አብዝቶ የሚጨነቀው፡፡ ከራሱ ቆርሶ ከጠብታው ቀንሶ አዲስ ህይወት ለመኖር ይተጋል፡፡ በርግጥ ግራሩ ደረቅ ነው፡፡ እንደ ሀረጊቱ የለመለሙ ቅጠሎች የሉትም፡፡ ቅርንጫፎቹ የተንጨፈረሩ ናቸው፡፡ ማራኪነት ይጐድለዋል፡፡ ይህ ውጫዊ ገፁ የኢየሱስን መልክ ያስታውሰናል፡፡ ‹የተናቀ የተጠላ ሠው ፊቱን ይሰውርበት ዘንድ እንዳችም የሚያስደስት ነገር የለውም›[8] ግራሩም እንዲሁ ነው፡፡

‹… ይኼ ክፉ ዘመን ቢያሸንፈው በረሃው ሕይወት ይዘራል ብሎ ስለሚያምን ነው› ግራሩ እምነት አለው፡፡ ማመን እና መታመን ደግሞ ለሰው ልጅ ብቻ የተሰጠ ረቂቅ ባህርይ ነው፡፡ እንስሶቹም ሆኑ አውሬዎች፤ ዛፎችም ሆኑ እፅዋት እምነት የላቸውም፡፡ ግራሩ የሚወክለው ባህርይ ግን እምነት አለው፡፡

> ‹‹… ቀኑ የሚሞተው በኛ ውስጥ ህይወትም የሚዘራው በኛ ውስጥ ነው፡፡ እኛ ካመንን ቅጠሎቻችን ተመልሰው ያን መዓዛ መልካቸውን ያመጣሉ፤ እኛ ካመንን ሰማዩ ወፍራም ደመና አዝሎ ይመጣል፡፡ ወንዞችም ተመልሰው ይፈሣሉ፡፡ እኛ ካመንን ወፎቹ ከዚህ ጠፍ ምድር ውስጥ አንሰራርተው ይነሱና ያንን መልካም ዜማቸው እንደገና እንሰማለን፡፡ ወፎቹ የሞቱት በኛ ውስጥ ነው፡፡ ወንዞቹም የደረቁት በኛው ደረቅ ነፍስ ውስጥ እንጂ ከውጭ አይደለም፡፡ እኛ ፀንተን ቆመን ካልጠራነው በራሱ የሚመጣ ደግ ቀን የለም፡፡ አሸንፈን ካላሳለፍነው በራሱ አውቆ የሚያልፍ ክፉ ቀን የለም፡፡›› (ገፅ 182)

ይህን አባባሉን ዙሪያው ያሉ ሰዎች አይረዱትም፡፡ አባባሉ ጥምዝ ቅኔ ይሆንባቸዋል፡፡ እሱ ግን እንዲህ ባለ እምነት መሞላቱ አጸናው፣ አፅናናው፡፡ ከዐለት

---

[8] ኢሣ 53÷6

ውስጥ ውሃ ጨምቆ ከመውሰድ ይልቅ ራሱን ያነፀበት እምነት አጠንክሮ አቁሞታል፡፡ ‹… የማይቻለውን ችሎ ከእምነቱ ውስጥ ህይወት ያለው ፍጡር እስኪወለድ ፀንቶ ሲጠብቅ ብዙ ዘመን አሳልፏል፡፡› (ገፅ 83)፡፡

ግራሩ ለሕይወት ፅኑ ፍቅር አለው፡፡ ‹… ሙታንን በፍቅሩ ብርታት ከራሱ እምነት ውስጥ ከመቃብር አሥነሳቸዋለሁ ብሎ ያምናል› (ገፅ 183)፡፡

ከብዙ ዓመት በኋላ፣ በግራሩ እምነት ምክንያት፤ የአፈሩ ሽታ ሲለወጥ፤ እምነት ሕይወት ስትወልድ፤ አንዲት ሐረግ መጣች፡፡ የሐረግዋ መምጣት የሕይወቱን አቅጣጫ ቀየረው፡፡ ከብርቱ የወይራና የሾላ ዛፎች ቀድማ ሞትን ድል በማድረጓ እጅጉን ደስ ተሰኘ፡፡ የተለየ ክብር እና ፍቅርም ሊሰጣት ወደደ፡፡

‹ይህን ክፉ ዘመን ተደጋግፈን እናሸንፈዋለን፤ አንቺን ስጠብቅ በዚህች ስፍራ ስንት ቁጣ ስንት መዓት አሳልፌያለሁ፤ በመጨረሻም ተስፋዬ ተወለድሺልኝ› (ገፅ 187)

ሁለቱ ገፀ ባህርያት - ግራሩና ሀረጉ - በምስያ ዘይቤ የተገለፁና የሰውን ባህርይ ተክተው የሚያስቡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ሀረግዋ እንደ ሰው ልጅ በረቂቅ ባህርያት የተሞላች ናት፡፡ የበረሃውን ስፋት ግራና ቀኝ ስታይ በፍርሃት ተውጣለች (ገፅ 187)፡፡ በግራሩ በኩል ከምታገኘው ውሃ ይልቅ ከአንደበቱ የምትሰማው የተስፋ ቃል ያለመልማት ነበር (ገፅ 188)፡፡ እየተመቻች ሲሄድ ግራሩ የዋለላትን ውለታ እንድትዘነጋ የሚያደርግ ክፉ መንፈስ በልቦናዋ ትፀንስ ነበር (ገፅ 189)፡፡ ሆደ ባሻ ናት፣ በየምክንያቱም ታኮርፋለች (ገፅ 192)፡፡ መቀየምን ታውቃለች፤ የክብርም ጉዳይ ያሳስባታል (ገፅ 192)፡፡ ግራሩም ቢሆን ሀረጓ ተለይታው ለመኖር ስትወስን ክፉኛ ደንግጧል (ገፅ 196)፡፡ እንዳትሄድም በሀዘን ተውጦ ይለምናታል (ገፅ 197)፡፡

ግራሩም -ሰውን ተመስሎ እየኖረ ነውና- የአገር ጉዳይ ግድ ይሰጠዋል፡፡ ሊኖርለት የሚፈልገው ህይወት አለው፡፡ ‹… በማያውቀው ረቂቅ ድርና ማግ የራሱና የአገሩ

ህይወት ተሳስሮበታል› (ገፅ 192)፡፡ ለሀረግ የሚያደርገው ነገር ሁሉ ለእገር የሚደረግ ውለታ ነው፡፡ ለሚያደርገው ነገር ደግሞ ወሮታ አይጠይቅም፡፡ የኖረ የሚመስለው ለሌሎች መኖር ለሌሎች መወለድ ሰበብ ሲሆን ነው፡፡ ‹… ለዚህ ተቀጥሎ ለደረቀ ምድር ለዚህ ክፉ ዘመን ለዚህ ለጠፉ አገራችን ጭምር አንቺ ታስፈልጊያለሽ፡፡ › (ገፅ 195)፡፡

ግራሩ አጥንት አለው፡፡ አጥንቱ ጠንካራ ነው፡፡ ቢደገፉት አይሰበርም፡፡ ሀረጓ የለመለመ ቅጠል አላት፡፡ ቅጠሉ ለስላሣ ነው፡፡ እንኳንስ ሊደገፉት ራሱንም ማቆም አይችልም፣ ግን ግራሩ የሌለው አንድ ነገር አላት፡፡ ከራስዋ አልፎ ለግራሩ የሚተርፍ ልብስ አላት፡፡ የግራሩ አጥንት ደግሞ ቀጥ ብላ እንድትቆም ከመቆምም አልፋ የግራሩ ቁመት ላይ ደርሳ ደረትዋን ለፀሃይ ማስጣት ጀምራለች፡፡ በትክክልም አንዱ ላንዱ ሕይወት ሰጥቶታል፤ ተስፋ አርግዞ እንዲወልድ አስችሎታል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በምሳሌ እንደታየው ይህም ‹ሀረግና ግራር› የተሰኘው አጭር ታሪክ አንድ አሊጎሪ ድርሰት ማሟላት የሚገባውን ባህርይ አሟልቷል ለማለት ያስችለናል፡፡ ገፀ ባህርያቱ እንደትዕምርት የሚወክሉት ነገር አላቸው፡፡ ግራሩ ፍሬን፣ ቤተሰብን ይወክላል፤ ለዚህም ነው ስለ ነገው ትውልድ የሚጨነቀው፡፡[9] ሀረጓ ግን ዛሬን ነው የምትወክለው አሁንም በሁለቱ መካከል ያለው ወዳጅነት እንደማያዛልቅ ተሰናክሎም እንደሚቀር ለማመላከት የተፃፈ ነው፡፡

---

[9] በFerber Michael የተፃፈውን A Dictionary of Literary Symbols የተባለውን መጽሐፍ ልብ ይሏል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያ

አሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት ረቂት ባህርያትን ማለትም ሞት እና ሕይወትን፣ ድንቁርና እና ዕውቀትን፣ ትህትና እና ትዕቢትን ብቻ ሳይሆን፣ ዕፅዋት እና አዝርዕትን፣ አራዊት እና እንስሳትን በማናገር፣ የሚቀርብ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት ነው፡፡ ይህ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት የሰው ልጅ የተሻለ ዓለም እንዲፈጥር ያነሣሣዋል፣ ራሱን፣ አካባቢውን፣ ፈጣሪውን እና የሚኖርበትን ዓለም እንዲያውቅ ያደርገዋል፡፡

አሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት፣ ብዙውን ጊዜ ረቂቅ ባህርያትን፣ ግዑዝ ፍጥረታትን እና እንስሳና አራዊትን ሰውኛ (personification) በማድረግ፣ በትረካው ውስጥ ትዕምርቶችን (symbols) በመጠቀም፣ ሊፈከር የሚችል (interpretation) ታሪክ በመፍጠር፣ የምልክቶችን (Signs) አገባብ ትርጓሜ በመስጠትና ተነፃፃሪ ዘይቤዎችን (Simile) በመጠቀም ፍቺ የሚሰጠው የሥነ ጽሑፍ ብልሃት ነው፡፡

በዓለም የሥነ ጽሑፍ ታሪክ፣ ይህንን የሥነ ጽሑፍ ብልሃት መጠቀም የተጀመረው፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት በነበሩ ደራስያንና በግሪኮች አማልክታዊ ሀተታ የሚጠቀስ ቢሆንም፣ እስካሁን ድረስ ብልሃቱን በመጠቀም ደራስያን ሃይማኖታዊ፣ ሞራላዊ፣ ሥነ ምግባራዊና ፖለቲካዊ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ እንደሚጠቀሙበት በዚህ ጥናቴ ለማሣየት ሞክሬያለሁ፡፡

በዚህ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት ተጠቅመው በዓለም ላይ ዕውቅናን ካተረፉ ደራስያን መካከል፣ ጆርጅ ኦርዌል ተጠቃሽ ሲሆን፣ ‹አኒማል ፋርም› በተሰኘ ድርሰቱ፣ በሶሻሊስት ስርዐት ላይ ተሳልቋል፡፡ ጆን ቡንያን የተባው ደራሲ ደግሞ ፒልግሪም ፕሮግረስ (የመናኙ ጉዞ በሚል ርዕስ ወደ አማርኛ የተመለሰ) በተሰኘ ድርሰቱ የክርስትናን ሃይማኖት ለመስበክ አሊጎሪን ተጠቅሟል፡፡

ወደ አገራችን ስንመጣ፣ ምንም እንኳን አሊጎሪ የሚለውን ቃል ወደ አማርኛ ተመልሶ፣ አቻ ፍቺው ፀድቆ፣ በሥነ ጽሑፍ ምሁራን ዘንድ ሲጠቀሙበት ባናይም፣

የሥነ ጽሑፍ ብልሃቱ ግን ለአገራችን ሥነ ጽሑፍ እንግዳ አለመሆኑን በጥናቴ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ የምትጠቀምበትንና ቅዱሳት መጻሕፍትን የምትተነትንበት የአንድምታ ትርጓሜም ከአሊጎሪ ጋር ዝምድና እንዳለውም ተገንዝቤያለሁ፡፡ ‹አንድምታ› ልክ እንደ አሊጎሪ፣ ትዕምርቶችን፣ ምልክቶችን፣ ሰውኛ ዘይቤንና ተነፃፃሪ ዘይቤን ይጠቀማል፡፡ በታሪኩ ውስጥ የሚጠቀሱት ባለልቦለዶች ለአንዳች ነገር ውክልና ከመቆማቸው በተጨማሪ በትረካው ውስጥ ሌላ ምስጢር ፈልፍለን እንድናወጣ የሚያደርግ በኢትዮጵያ ባህላዊ ትምህርት የሚዘወተር የትርጓሜ ብልሃት ነው፡፡

ምንም እንኳን በተደጋጋሚ ጊዜ በአጥኚዎች ዘንድ የሚጠቀሰው ‹ወዳጄ ልቤ› ተብሎ የሚጠራውን የፈጠራ ሥራ አሊጎሪያዊ ባሕርይ መተንተን ቢሆንም፣ በአማርኛ ዘመናዊ አሊጎሪያዊ አጫጭር ልቦለዶችን በሚመለከት የተሰራ ጥናት ለማግኘት አልቻልኩም፡፡

በዚህም የተነሣ ‹አሊጎሪ ዘመናዊ በአማርኛ አጫጭር ልቦለዶች› በሚል ርዕስ ጥናቴን ስሰራ፣ ዘመነኛ እና በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ተጠቃሽ የሆኑ ደራስያን፣ አሊጎሪን እንዴት እንደተጠቀሙበት አይቻለሁ፡፡

አሊጎሪያዊ ልቦለዶች ናቸው፣ ምንንቱን ይገልፃሉ፣ ባህርያቱን ያሟላሉ ብዬ በዚህ ጥናት ያካተትኳቸው ደራስያን አምስት ናቸው፡፡ ከአምስቱ ደራስያን ሁለቱ ማለትም አዳም ረታና ስብሃት ገ/እግዚአብሔር ሁለት ሁለት፣ አሣምነው ባረጋ፣ ዓለማየሁ ገበየሁና ሚካኤል ሺፈራው ደግሞ አንድ አንድ ሥራዎቻቸው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ‹አሊጎሪ በዘመናዊ የአማርኛ አጫጭር ልቦለዶች› በሚለው ጥናቴ አስር አጫጭር ከአሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት አንጻር ተተንትነዋል፡፡

የአጫጭር ታሪኮቹ ምንጭም ከስብሃት ገ/እግዚአብሔር ‹አምስት ስድስት ሰባት› መድበል ውስጥ ‹አውራ ዶሮ› እና ‹ቢራቢሮ› የተሰኙትን፣ ከአዳም ረታ ‹ማኅሌት› መድበል ውስጥ ‹የአበቦች ታሪክ›ንና ከ‹አለንጋና ምስር› መድበል ውስጥ ‹የድንች

መዋስዕት› የተሰኘውን፣ ከአማምነው ባረጋ ‹የትሮይ ፈረስ› መድበል ‹የአራዳው ወንበር›ን ፣ ከአለማየሁ ገበየሁ ‹የሀበሻ ፊት› መድበል ‹አስቸኳይ ጉባኤ›ን እና ከሚካኤል ሺፈራው ‹የወፍ ማስፈራሪያ› መድበል ‹ሐረግና ግራር› የተሰኙ አጫጭር ልቦለዶችን፣ ከአሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት አንፃር ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ደራስያን በሥራዎቻቸው ውስጥ አሊጎሪን በተለያዩ መልኩ እና ለተለያዩ አገልግሎቶች ተጠቅመውበታል፡፡ የስብሃት ገ/እግዚአብሔር አጫጭር ልቦለዶች ‹ቢራቢሮ›ን ‹አውራ ዶሮ›ን ሰውኛ በማድረግ፣ ነፍስን (ህይወትን) እና ማንቂያ ደወልን እንደ ትዕምርት ተጠቅሟል፡፡ የአዳም ረታ አጫጭር ልቦለዶች ውስጥ ‹አበባንና ንፋስን› ትዕምርታዊ በሆነ መንገድ ‹እንደ ውብ ልጃገረድ እና እንደ ሃይለኛ ጉረምሳ› ተስለው ቀርበዋል፡፡ የሚካኤል አጭር ልቦለድም ‹ዛፍ›ን በመጠቀም የቤተሰብና የቋሚ ሕይወት ውክልና በመስጠት ሀረግና ግራርን ሰውኛ ባህርይ አላብሶ፣ ለሌሎች በሕይወት መቆየት ራስን አሣልፎ መስጠት እንዴት እንደሚገባ መንፈሳዊ ትምህርት አስተላልፎበታል፡፡ የአማምነው ባረጋ አጭር ልቦለድም ‹ወንበር› ፍትህ የተነፈገና በመጨረሻም ራሱን ለበቀል ያነሳሳ ዙፋንን ወክሎ፣ የሰውን ልጅ አስተዳደር ይተቻል፡፡ በአለማየሁ ገበየሁ አጭር ታሪክ ውስጥ የምናገኛቸው ወራት፣ ሰውኛ ተደርገው፣ ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት የሚታገሉ እንዲሁም ውስጥ ውስጡን ለሊቀ መንበርነት የሚሽቀዳደሙ ገፀ ባህርያት የተስተናገደበት ሲሆን፣ ታሪኩ ፖለቲካዊ አሊጎሪ የሚሰኝ ነው፡፡

በአጠቃላይ፣ ‹አሊጎሪ በዘመናዊ የአማርኛ አጫጭር ልቦለዶች› በሚለው ጥናቱ ውስጥ የተካተቱ ገፀ ባህርያት፣ የአሊጎሪን ምንነት ያወቁ ማለትም ሰውኛ ዘይቤን በመጠቀም፣ ትዕምርቶችንና ምልክቶችን በታሪኩ ውስጥ በማስገባት ፍቺ እንዲኖራቸው በማድረግና ከተፃፈው ታሪክ ውስጥ ሌላ ምስጢራዊ እና የተደበቀ ትርጓሜ እንዲይዙ በመቀመር የተፃፉ ሲሆኑ፣ አጫጭር ልቦለዶቹ ከአሊጎሪ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት አንፃር ሲተነተኑ፣ የአሊጎሪን ባህርያት የሚያሟሉ ሆነው አግኝቼያቸዋለሁ፡፡

## ዋቢ ጽሁፎች

ሀዲስ አለማየሁ፡፡ *ተረት ተረት የመሠረት፡* አዲስ አበባ፡ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡1985 ዓ.ም፡፡

መክብብ ደስታ፡፡ *ያቶ መለንበት ባልንጀርነት ታሪክና የምስጋና ግጥም* ፤ አዲስ አበባ፡ 1926 ዓ.ም፡፡

ማኅተመ ሥላሴ ወልደመስቀል፡፡ *ባለን እንወቅበት፡* አዲስ አበባ፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡ 1961 ዓ.ም፡፡

ሚካኤል ሽፈራው ፡፡ *የወፍ ማስፈራሪያ እና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች፡* አዲስ አበባ ፡ብራና ማተሚያ ድርጅት፡ 2000 ዓ.ም፡፡

ሠይፈስላሴ ዮሐንስ፡፡ "የአንድምታ ትርጓሜ በኢትዮጵያ ባህልና ትምህርት"፡ *Ethiopian Review of culture*. vol., XOV, 2011. አዲስ አበባ፡ ፋር ኢስት ትሬድንግ፡ 2004 ዓ.ም፡፡

ሳሙኤል አዳል፡፡ «ወዳጄ ልቤና አሊጎሪያዊ የሥነ ጽሑፍ ብልሃት»፤ ብሌን፡፡ የኢትዮጵያ ደራስያን ማሕበር መጽሔት፡ አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ፡1994 ዓ.ም፡፡

ስብሃት ገብረ እግዚአብሔር፡፡ *አምስት ስድስት ሰባት፤* አዲስ አበባ፡ ማህሌት አሳታሚ፡ 1998 ዓ.ም፡፡

ብርሃኑ ገበየሁ፡፡ *የአማርኛ ሥነ ግጥም* ፤ አዲስ አበባ፡ አልፋ አታሚዎች፡ 1998 ዓ.ም፡፡

ተሻገር ውቤ፡፡ *አቤቱታ፡* አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡ 1958 ዓ.ም፡፡

አለማየሁ ሞገስ፡፡ *የአማርኛ ግጥምና ቅኔ ማስተማሪያ፡* አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡ 1954 ዓ.ም፡፡

አሳምነው ባረጋ፡፡ *የትሮይ ፈረስ እና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች፡* አዲስ አበባ 1995 ዓ.ም፡፡

አስፋው ዳምጤ፡፡ «የአማርኛ ልቦለድ ጉዞ»፡ *መድበለ ጉባኤ፡* አዲስ አበባ፡ የኢትዮጵያ ደራስያን ማሕበር፡ 2001 ዓ.ም፡፡

አያልነህ ሙላቱ፡፡ *የሥነ ጽሑፍ ቅኝት፡* አዲስ አበባ፡ ንግድ ማተሚያ ቤት፡ 1977ዓ.ም፡፡

አዳም ረታ፡፡ *ማህሌት፡* አዲስ አበባ፡ ማህሌት አሳታሚ፡ 2002 ዓ.ም፡፡

______________:: *ለለንጋና ምስር*፤ አዲስ አበባ፣ ማህሌት አሳታሚ፣ 2002 ::

አጥናፍሰገድ ይልማ:: *የእንስሳት ዐመፅና ድርድር*፤ አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬድንግ ኃላ.የተ.የግ.ማሕበር፣ 2003 ዓ.ም::

እምሩ ኃይለሥላሴ:: *ሰውና እውቀት*፤ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1948 ዓ.ም::

ኅሩይ ወልደስላሴ:: *የልብ አሳብ፤ የብርሃኔና የጽዮን ሞገሴ ጋብቻ*፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንን ሰላም ማተሚያ ቤት፣1923 ዓ.ም::

______________:: *ወዳጄ ልቤ*፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንን ሰላም ማተሚያ ቤት፣1915::

ገብረእየሱስ ሃይለማርያም:: *የአካላት ሴራ*፤ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1985 ዓ.ም::

ጌቴ ገላዬ:: ‹‹አሊጎሪና ተምሳሌት በአማርኛ ልቦለድ ውስጥ››፤ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ፣ 1984 ዓ.ም::

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር:: *መጽሐፍ ቅዱስ*፤ አዲስ አበባ፣ 1980 ዓ.ም::

ያየህይራድ ወንጌሌ:: *መጭው ዘመን፡ የጥፋት ርኩሰት እና የድኅነት ጥበብ*፤ አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም::

ዮናስ አድማሱ:: ‹‹የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ››፤ *መድበለ ጉባኤ*፤ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር፣ 2001 ዓ.ም::

______________:: ጦቢያ ‹‹የንባብና የትርጓሜ ነገር ዘይቤ፤ የጦቢያ ምሳሌ››:: አምስተኛ ዓመት፣ ቁጥር 39፣ 1989 ዓ.ም::

ዘሪሁን አስፋው:: *የሥነጽሑፍና መሠረታውያን::* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም::

______________ :: *ልብ ወለድ አዋጅ እና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች ከቀደምት የኢትዮጵያ ደራስያን (1898-1948)*፡ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1995 ዓ.ም::

Amelia, A. Zurcher. *Seventeenth-century English Romance*: Allegory, Ethics, and Politics. USA; Macmillan India Ltd., 2007.

Baldick, Chris. *The Concise Oxford Dictionary of Literary Terms.* New York;

Oxford University Press Inc., 2001.

Bennett, Andrew and Nicholas Royle. *An Introduction to Literature, Criticism and Theory.* Great Britain: Pearson Education Limited, 2004.

Danesi, Marcel. *Messages, Signs, and Meanings: A Basic Textbook in Semiotics and Communication Theory*, 3rd Ed. Toronto; Canadian Scholars' Press Inc, 2004.

Ferber, Michael. *A Dictionary of Literary Symbols.* New York: Cambridge University Press, 2007.

Rose H. *A Handbook of Greek Mythology.* London and New York: Routledge, Taylor & Francis Group, 2005.

Spargo R., Clifton and Robert M. *After Representation: The Holocaust, Literature, and Culture.* London: Rutgers University press, 2010.

Suttie Paul. *Self-Interpretation in The Faerie Queen.* Cambridge; D. S. Brewer Ltd, 2006.

Orwell, George. *Animal Farm*, Penguin Modern Classics, 1945.

ይህ አሊጎሪ በአማርኛ ዘመናዊ አጫጭር ልቦለዶች የተሰኘው የጥናት ጽሁፌ ኦሪጅናልና ከዚህ ቀደም በየትኛውም ዩኒቨርሲቲ ያላቀረብኩት እና በዚህ የጥናት ጽሁፍ የተገለጹ መረጃዎች በሙሉ ምንጫቸውን የ[illegible]ጠቀስኩ መሆኔን ልገልጽ እወዳለሁ፡፡

እንዳለጌታ ከበደ

ፊርማ ______________________

አዲስ አበባ

ቀን ፡- የካቲት 28/2004 ዓ.ም